ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፣
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዝእተብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

**ቍጥር ፲፰/፳፻፱ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**

**በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥ ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡**

**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**

**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።**

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤
እግዝእተብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤
በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥
እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ካህናችን፥
ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡
በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

**+ + +**

## ይድረስ፡-

**በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥**
**በልጁ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥**
**በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡**
**የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥**

**ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና**
**በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥**
**በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥**
**በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥**

**ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡**
**የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡**
**"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡**
**በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥**

**በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡**
**የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡**
**ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!**
**እንዲሁም፡**
**የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡**
**በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥**
**ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥**
**በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!**

**በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!**

# መቅድም

በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ቃል ከተነገረው፣ ካለፈው፡ ከ፲፯ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ በፊት፡ ይፋ እንደወጣው፡ እንደ፲፰ኛውና ከእርሱ እንደቀደሙት ተከታታይ መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎቼ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዝእተብሔራችሁና ሃይማኖታችሁ፥ መድኃኒታችሁና ክህነታችሁ፥ እናታችሁና ንግሥታችሁ፥ አገራችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ።**

## የዚህ ዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ ምክንያት፡

ለዚህ፡ ለአኹኑ የዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ የኾነው ምክንያት፡ ለእውነተኞች ልጆቻችን፡ ለመናገርም፣ ለመስማትም፡ ሊያሠቅቋችሁ የሚችሉ፣ ነገር ግን፡ ሓሰት በመኾናቸው፡ በእኛዪቱ እግዚአብሔራዊት እውነት፡ አማናዊነታቸው የተነገረላቸው ኹለት ቍም-ነገሮችን ስለያዘ፡ አርእስተ-ጉዳይ ነው፤ እርሱም፡-

፩ኛው፡ "ገድለ-አዳም" በሚል ርእስ፡ አብነቱ የኾነውን ግእዙን፡ ወደኢትዮጵያኛ [ዐማርኛ] የተረጐመው፡ "መምህር ተስፋ-ሚካኤል ታከለ" የተባለ ሰው ኾኖ፡ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ፣ ማኅበረ-ቅዱሳን፣ በ፳፻፫ ዓ.ም. ታትሞ በተሠራጨ መጽሓፍ ውስጥ፡ ቅዱሱን የባል እና ሚስት ሩካቤ-ሥጋን ምግባር፡ *"የእኛን የእግዚአብሔርን ሕግ እንደማፍረስ የሚያስቆጥርና ራሱም፡ እንደዝሙት የሚቆጠር፡ የኃጢኣት ግብር ነው!"* በሚያሰኝ አገላለጽና አቀራረብ፡ *የሩካቤ-ሥጋን አደራረግና አፈጻጸም፡ ለአዳም እና ለሔዋን ያሳዩዋቸውና ያስተማሯቸው "ሰይጣናት ናቸው!"* የሚለው ሓሳዊና እኩይ፡ ነገረ-ጽሕፈት ነው።

፪ኛው፡ "በቅዳሴ ጊዜ፡ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ ያወኩትን፡ ሕፃናተ-ገምኑዲን 'አጥፉ!' ብለን፡ እኛ እግዚአብሔር፡ መላእክትን እንደሰደድን፣ የቀሩት መላእክት፡ የተላኩበትን ግዳጅ ፈጽመው ሲያርጉ፡ 'ቀውስጦስ' የሚባለው አንዱ መልአክ ብቻ፡ አንዱን መልከ-መልካም ሕፃን ከነማርዳው አግኝቶ፡ 'ይህንስ፡ የፈጠረው ይግደለው!' ብሎ ሳይቀሥፈው ስለተወው፡ በዚህ የተልእኮ ጉድለቱ፡ መልአካዊው ኃይል ተነሥቶት፡ ማረግ ሳይቻለው በመቅረቱ፡ በእኔ ተማሕፅኖ፡ መለኮታዊዉን ምሕረት አግኝቶ፡ እንደገና፡ ወደሰማይ የማረግ ብቅዓቱ እንደተመለሰለት ተደርጎ፣ በቅዳሴ ማርያም፡ የአንድምታ ትርጓሜ መጽሓፍ ውስጥ የተተረከው፡ ዝክረ-ነገር ነው፤

ካህኑ [አገልጋዩ] ልጃችን ኤርምያስ፡ እነዚህን ኹለት ጠንቀኛ ስሕተቶች፡ ሰዎች በደረሷቸው፡ በእነዚያ መጻሕፍት ውስጥ፡ በግልጽ ሠፍረው ዐይቶ በማንበቡ፡ በጥልቅ አዝኖ፡ ወደእኔ ስላመለከተኝ፡ ይህንኑ አርእስተ-ጉዳይ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን ብቻ ሳይኾን፡ ለመላዎቹ ሰዎች ፍጡሮቻችን ጭምር፡ እኔው ራሴ እንዳብራራላቸው የሚያስፈልግ፤ ይህንም ለማድረግ፡ የእኔው፡ የራሴ ፈቃዴም ኾኖ ተገኘ።

ፈቃዴና አስፈላጊ የኾነውም፡ በአንድ በኩል፡ እየራሳቸውን፡ በስሜ፡ "ኢትዮጵያውያን" እና "ኢትዮጵያውያት" ብለው የሚጠሩ፤ እኔ ግን፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ በሥውርና በገሃድ፤ በድፍረትና በይፋ በፈጸሙት፡ ክህደትና ዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትና በብዙው የተለያየ ኃጢአታቸው ምክንያት፥ ከዚያ ክፋታቸውም፡ በንስሓ ለመመለስ፡ ፈቃደኞች ኾነው ባለመገኘታቸው፡ "ልጆቼ" ልላቸው ያልተቻለኝ፡ የሰው ወገኖች፡ ያን የመሰለውን ታላላቅ ጥፋት፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ ስለቀጠሉበት ነው፤

በሌላው በኩል ደግሞ፡ እነዚያኞቹ፡ ያን፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትና የተለያየ የኃጢኣት ድርጊታቸውን ይዘትና ኺደት፡ በደንዳናነት በቀጠሉበት ሰዓት፡ ታማኞቹ ልጆቻችን የኾኑት ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት እና ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን ግን፡ "አንቀበለውም!" ብለው፡ ያስታወቁትን፤ እኔም፡ በዚህ ረገድ፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር የኾነችውን እውነት፡ እነርሱ ብቻ ሳይኾኑ፡ ሌሎቹም፡ የሰው ፍጥረት ወገኖች የኾኑ፡ ወንዶቹም ኾኑ፤ ሴቶቹ፡ ኹሉም፡ ለአእምሮቸው ግልጽ ኾኖላቸው፤ በሃይማኖት ተቀብለውትና በምግባር አጽንተውት፤ ሕይወትም አድርገውት ይኖሩት ዘንድ፡ እንዲቻላቸው ለማድረግ ነው።

በቀደመ ነገር፡ የእኔ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የእኛ የእግዚአብሔር የኾነውን ማናቸውንም ነገር፡ በየልባቸው ጽላት ላይ እንደጻፍነው፡ እንደዚያው እንዳለ ይጠብቁታል እንጂ፤ እንደባዕዳኑ የሥጋና የመንፈስ ገዢዎቻቸው፡ በክርታስ ሰሌዳ ላይ፡ በእጅ ብዕር አይጽፉትም። መጻፍ ቢያስፈልጋቸውም፡ ያንኑ የእግዚአብሔሩን እውነት፡ ሳይቀንሱም፥ ሳይጨምሩም፡ እንዳለ ይጽፉታል እንጂ፡ የሚያዛቡት አንዳችም ነቊጥ፡ ከቶ የለም።

ታዲያ! እነዚህ ክፉዎች ባዕዳን ቅኝ ገዢዎቻችሁ፡- እነርሱም፡ በአንድ በኩል፡ የቀደሙት፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ ካህናትና ሊቃነ-ካህናት ሲኾኑ፤ በሌላው በኩል ደግሞ፡ የኋላ ኋላ፡ እነርሱን ተከትለውና ተክተው የመጡባችሁ፡ ኦርቶዶክሳውያኑ፡ የግብፅ መነኮሳትና "ጳጳሳት"፡ ይህን ኹሉ ጉድ፡ በቃል ሲነግሩዋችሁ፤ በመጽሓፍም ከትበው ሲሰጧችሁ፤ እናንተም ስታነብቡት፡ ይህን የሓሰት ወሬ፡ እንዴት አምናችሁ ተቀበላችሁት? <u>ይህን የነውርና የጭካኔ ድርጊት፡ እንኳንስ እኛ ፈጣሪያችሁ፡</u> እናንተም ኾናችሁ፤ ወይም፡ ከእናንተ የከፉት አረመኔዎች እንኳ፡ "ያደርጉታል!" ብላችሁ፡ የምታስቡት ነውን? አይደለም። እናንተ ቀርታችሁ፡ እነርሱም እንኳ አያስቡትም።

*መምህራችሁ፣ ልጁ ወዳጁ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡- "**መኑ ውእቱ እምኔክሙ፡ ዘይስእሎ ወልዱ፡ ኅብስተ፣ ወእብነ ይሁቦ? ወእመሂ ዓሣ ሰአሎ፡ አርዌ-ምድርኑ ይሁቦ? ወእመኒ አንቆቅሖ ሰአሎ፡ ዐቅረበኑ ይሁቦ ህየንቴሁ? ወሶበ እንዘ እኩያን አንትሙ፡ ተአምሩ ሠናየ ሀብተ ውሂበ ለውሉድክሙ፣ እፎ ፈድፋደ፡ አቡክሙ ዘበሰማያት፡ ይሁብ ሠናየ ሀብተ መንፈስ-ቅዱስ፡ ለእለ ይስእልዎ!***

*"ከእናንተ መካከል፡ ማነው፡ ልጁ፡ "ዳቦን ስጠኝ!" ብሎ ቢለምነው፡ ድንጋይን አንሥቶ ይሰጠዋልን? ወይስ፡ ዓሣን ቢለምነው፡ እባብን ይሰጠዋልን? ወይስ ደግሞ፡ እንቁላልን ቢለምነው፡ በዚያ ፋንታ፡ ጊንጥን ይሰጠዋልን? እንግዴህ፡ እናንተ፡ ክፉዎች ስትኾኑ፡ ለልጆቻችሁ፡ ደጎች ኾናችሁ፡ እንዲህ፡ መልካሙን ስጦታ ማበርከትን የምታውቁ ከኾናችሁ፡ ታዲያ! የሰማዩ አባታችሁና እናታችሁማ፡ ለሚጠይቋቸው ኹሉ፡ ታላቁን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ እንዴት አብዝተው አይሰጧቸው!? ይሰጧቸዋል እንጂ።" ብሎ ያስተማራችሁን፡ በተለይ እናንተ፡ እንዴት ዘነጋችሁት? (ማቴ. ፯፥ ፱-፲፩፤ ሉቃ. ፲፩፥ ፲፩-፲፫።)*

*ይኹን እንጂ፡ ክፉዎቹ እና ሓሳውያኑ ቅኝ-ገዢዎቻችሁ፡ በየመጽሓፎቻቸው ከትበው የሰጧችሁን፡ ያን፡ የነውርና የጭካኔ ድርጊት የመላበትን፡ ያፈጠጠና ያገጠጠ ሓሰት፡ እናንተም፡ እንዲህ፡ አምናችሁ ልትቀበሉትና ልትፈጽሙት ከቻላችሁ፡ እናንተም፡ እንደነርሱ፡ "የሓሰት ልጆች" መኾናችሁ አይደለምን? አዎን! በእርግጥ፡ እናንተም፡ እንደነርሱ፡ "የሓሰቱ፡ የዲያብሎስ ልጆች" መኾናችሁ እኮ ነው።*

## ክፍል አንድ።

## *ለዚህ ኹሉ፡ የአይሁድና የግብፃውያን ጠንቀኛ ክፉ ግብር፡ ቀዳሚው ማስረጃ።*

*ለነገሩ፡ ይህን የመሰለው ጠንቀኛ ደባ፡ በአስተዋዮቹና በታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ እንግዳ መርዶ ኾኖ የሚታሰብና የሚነገር፣ አይደለም። በትውልዱ ዕብራዊ፣ በማንነቱ ግን፡ ኢትዮጵያዊ የኾነው፡ ደጉ አገልጋያችን ሙሴ ጽፎት፡ በመላው ዓለም የሰዎች ቋንቋዎች ተተርጉሞ በሚነበበው፡ እናንተ፡"ቅዱስ" በምትሉት መጽሓፋችሁ አማካይነት፡ በዓለሙ ኹሉ ሕዝቦች ዘንድ፡ እስካኹን፡ "እውነት ነው!" ተብሎ ብቻ ሳይኾን፡ "የእግዚአብሔር ቃል ነው!" ተብሎም፡ ሃይማኖታዊ እውነተኝነቱ ተረጋግጦለት፣ ተቀባይነትንና ተአማኒነትን አግኝቶ፡ ይኸው፡ በይፋ የሚታወቅ ኾኖ፣ ሲደመጥና ሲፈጸም የኖረ ገሃድ እውነታ ነው።*

በአንድ በኩል፡ እኛው እግዚአብሔር፡ በሠራነው፣ ራሳችንም በሠራንበት፡ በቅዱሱ የጋብቻ ሥርዓታችን ተጋብተው፡ ቅዱሱን ሩካቤ-ሥጋን፡ በቅድስና በመፈጸም፡ ልጆችን እንዲወልዱና እንዲባዙ፡ የእኛን አምላካዊና ተፈጥሮአዊ ዕውቀት አቀዳጅተን፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ በመልካችንና በአርአያችን የፈጠርናቸው አዳምና ሔዋን፡ በገዛ ራሳቸው የስምምነት ፈቃድና ውሳኔ እንዲፈጽሙት፡ በሰጠናቸው ሥልጣን፡ እነርሱው የሚያዝዙበት ቅዱሱ ሩካቤ ሥጋ፡ እንደርኵሰት ተቆጥሮ፡ እርሱዉንም <u>"ያስተማሯቸው፡ ሰይጣናት ናቸው!"</u> ተብሎ፡ በሃይማኖታዊ እውነተኝነቱ ተቀባይነትን አግኝቶ፣ ተጽፎም፡ እነሆ፡ ሲነበብና ሲሰማ ይገኛል።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ ዓቅመ-ቢሶች የኾኑ ሕፃናትና አዛውንት፣ ወንዶችና ሴቶች ሳይቀሩ፡ በጦር እየተወጉና በሰይፍ እየታረዱ፥ በእሳት እየተቃጠሉና ገደል እየተጣሉ እንዲያልቁ፡ በነቢያቶቻችን አማካይነት እያዘዝን፣ እንዲህ ያለው፡ ጭከናና ግፍ፡ በሕያዉ ሰብአዊ ፍጥረታችን ላይ፡ ያለማቋረጥ እየተካኼደ እንዲፈጸም፣ ከዚህ የተነሣም፡ ይህ ኹሉ ዕልቂትና ደም-መፍሰስ፡ እንዲደርስ ስናደርግ የኖርነው፡ <u>"እናንተው ራሳችሁ እግዚአብሔር ናችሁ!" ተብለን፣</u> ይኸው ወንጀላችን፡ በቃል ብቻ ሳይኾን፣ በጽሑፍም ተረጋግጦብን፣ በይፋም እንዲታወቅ ተደርጎ ይገኛል።

ለመኾኑ፡ ይህን ኹሉ የሓሰት ውንጀላ፡ በእኛ በእግዚአብሔር ላይ የሠነዘረ ማን ነው? እነዚሁ፡ ኦሪታውያኑ የአይሁድ ካህናትና ሊቃነ-ካህናት፣ ኦርቶዶክሳውያኑ፡ የግብፅ መነኮሳትና ጳጳሳት አይደሉምን? አዎን! ናቸው። ይህንኑ፡ የሓሰት ውንጀላቸውን አረጋግጠው ለማሳወቅ የሞከሩትስ፡ እንዴትና በምንድር ነው?

አረጋግጠው ለማሳወቅ የሞከሩትማ! ይህንኑ ዝክረ-ነገራቸውን በሚመለከት፡ በብዛትና በስፋት፥ በምልዓትና በጥልቀት አቀናብረው ያዘጋጁትን ዜና መዋዕላቸውን፡ በጽሑፍ አሥፍረውበት በሚገኘው፣ "ብሉይ-ኪዳን" በተባለውና የዚሁ መጽሓፍ ቅዱሳችሁ፡ የመጀመሪያው ክፍል በኾነው ክታባቸው፣ በሌሎቹም የአዋልድ ድርሳኖቻቸው መኾኑን፡ ኹሉም የሰው ወገን፣ እናንተ ጭምር ታውቁታላችሁ።

በዚህ ረገድ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የበቃው፡ ደጉ አገልጋያችን ሙሴ፡ በእግዚአብሔራዊቷ እውነትና በመንፈስ ቅዱስ እምነት ስለሚፈጸመው አምልኮተ-እግዚአብሔር፡ ከኢትዮጵያዊው ካህናችን አማቹ ዮቶር እና እኛ እግዚአብሔር፡ ሚስቱ ትኾን ዘንድ ከሰጠነው፡ ከኢትዮጵያዊቷ ልጃችን፡ ከሲጳራ ባገኘው መለኮታዊ ዕውቀቱ፡ በሰማይና በምድር ተጀምሮ፡ በአዳምና በሔዋን ስላበቃው ሥነ-ፍጥረት በጻፈው፡ <u>በኦሪት ዘልደት፡ ከምዕራፍ ፩ እስከምዕራፍ ፲ ከመዘገበው በቀር፣</u> ሌላው በሙሉ፡ እነዚሁ፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" እያሉ፡ በግብዝነት፡ ስለሚመጻደቁበት፣ ስለራሳቸው ማንነትና ምንነት የጻፉት እንጂ፡ የእኤዎቹን የኢትዮጵያን ልጆች ዜና-መዋዕልና ዝክረ-ነገር የሚመለከት፣ አንዳችም አንቀጽ የሚገኝበት አይደለም።

ዐልፎ ዐልፎ ቢኖርበትም እንኳ፡ ያውም፡ በእነርሱው በጸሓፊዎቹ እጅ፡ ኹን ተብሎ፤ እንዲዛነፍና እንዲቃወስ፣ እንዲጓደልና እንዲፃረር የተደረገ ነው። በጽሒፈቱም፡ የእኔዎቹ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የተሳተፉበት አይደለም።

ቀደም ብዬ የጠቀስሁት፡ በኦሪት ዘልደት [ዘፍጥረት]፡ ከምዕራፍ ፩ እስከምዕራፍ ፲ የተመዘገበውና በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ትውፊት ተጠብቆ የኖረው፡ የሥነ-ፍጥረት ቃለ-እግዚአብሔርም ቢኾን፡ ከደባው ጠንቅ ያልጸዳ መኾኑ፡ ለማንኛችሁም፡ አስተዋዮች ለኾናችሁ ሰዎች ፍጡሮቻችን፣ በተለይም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ያሰኛችሁን ማንነታችሁን አጽንታችሁ ለኖራችሁት፡ ለኢትዮጵያ ልጆቼ በግልጽ የሚታወቅ ነው።

ይኸውም፡ በ፱ኛው ምዕራፍ፥ ከቍጥር ፳ እስከ፳፯ ያለው አንቀጽ፡ ስለኖኅ ስካር፣ ኖኅም፡ "በኵሽ እና በልጁ፡ በከነዓን ላይ ተናገረ!" ስለተባለው ርግማን የሚተርከው፡ ከእነዚሁ፡ ከክፉዎቹ ኦሪታውያን አይሁድ፡ በሓሰት፣ ኹን ተብሎና ተጨማሪ ኾኖ፡ በእመጫትነት የታከለው፡ ልብ-ወለድ ታሪክ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ያ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ጸንቶ የኖረው፡ የሥነ-ፍጥረት ጥቅስ፣ እርሱም፡ በኦሪት ዘልደት፡ ከምዕራፍ ፩ እስከምዕራፍ ፲ የተመዘገበው፣ ይህን፡ የሓሰተኞቹን ኦሪታውያን አይሁድ፡ ልብ-ወለድ ታሪክ የማያጠቃልል መኾኑን፡ ኹሉም፡ በጥብቅ ሊገነዘበው ይገባል።

በሓሰተኞቹ ኦሪታውያን አይሁድ የተጻፈውን፡ ይህንኑ፡ ሓሳዊና መሠሪ የኾነውን፡ የልብ-ወለድ ታሪክ፡ ይኸው ስሙት! እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው፡-

"ወእምድኅረ አይኅ፡ አኀዘ ኖኅ ይትገበራ ለምድር፤ ወተከለ ዐፀደ-ወይን። ወሰትየ እምኔሁ፤ ወሰከረ፤ ወተዐርቀ፡ በውስተ ቤቱ።

"ወርእዮ ካም፡ አቡሁ ለከነአን፡ ዕርቃነ አቡሆሙ። ሰሓቀ፤ ወወፅአ፤ ወነገሮሙ ለክልኤሆሙ አኀዊሁ፡ በአፍኣ።

"ወነሥኡ፡ ሴም፥ ወያፌት፡ ልብሰ፤ ወወደዩ ላዕለ ክልኤሆሙ፡ ዲበ ዘባናቲሆሙ፤ ወሖሩ ድኅሪተ፤ ወከደኑ ዕርቃነ-አቡሆሙ፤ ወገጾሙ ድኅሬሆሙ፡ አግብኡ፤ ወኢርእዩ ዕርቃነ-አቡሆሙ።

"ወሶበ ጽሕወ ኖኅ፡ እምስካረ ወይኑ፡ አእመረ፡ ኵሎ ዘገብረ ሎቱ፣ ወልዱ፡ ዘይንእስ።

"ወይቤ ኖኅ፡- 'ርጉመ ለይኩን ከነአን! ወገብረ፣ ወነባሬ ይኩን፡ ለአኀዊሁ! ወይቤ፡- 'ይትባረክ እግዚአብሔር፡ አምላኩ ለሴም! ወይኩን ከነአን፡ ገብሮ! ወለያርኅብ እግዚአብሔር፡ ብሔሮ ለያፌት! ወይኅድር ውስተ ቤቱ ለሴም! ወይኩን ከነአን፡ ገብሮ!

"ከጥፋት ውኃ በኋላም፡ ኖኅ፡ ምድርን ይቈፍር ጀመረ፤ የወይን ተክልንም ተከለ። ከተጠመቀው የወይን ጠጁም ጠጥቶ ሰከረ፤ በቤቱም ውስጥ ዕራቁቱን ኾነ።

"የከነአን አባት ካምም፡ የአባታቸውን ዕርቃን አየ፤ ሳቀም፤ ወደውጭ ወጥቶም፡ ለኹለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው።

"ሴምና ያፌትም፡ ልብስ ወስደው፡ ኹለቱም በየትከሻቸው ላይ አደረጉ፤ የኋሊትም ኼደው፡ የአባታቸውን ዕርቃን ሸፈኑ፤ የኋሊት የነበረ ፊታቸውንም ሳያዞሩ፡ ተመልሰው ስለወጡ፣ የአባታቸውን ራቁትነት አላዩም።

"ኖኅም፡ ከወይን ጠጁ ስካር በነቃ ጊዜ፡ ታናሹ ልጁ ያደረገበትን ኹሉ ዐወቀ። አለም፡- 'ከነአን፡ የተረገመ ይኹን! ለወንድሞቹም፡ ባሪያ፣ ተገዢም ይኹን!' አለም፡- 'የሴም ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን! ከነአን፡ ባሪያው ይኹን! እግዚአብሔር፡ የያፌትን አገር ያስፋ! በሴም ቤትም ይደር! ከነአንም፡ ባሪያው ይኹን! (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፱፥ ፳-፳፯።)

## ይኸው ልብ-ወለድ ታሪክ፡ ሓሳዊነቱንና መሠሪነቱን፡ በራሱ ሲመሰክር።

እኒህ፡ የቀደሙት ክፉዎች አሪታውያን አይሁድ፡ ይህን ሰይጣናዊና ጠንቀኛ፣ ሓሳዊና ልብ-ወለድ የኾነ ታሪክ የፈጠሩት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ይህንም ምክንያት፣ ሓሰተኛነቱንም ከሚያሳዩት፡ ከብዙዎቹ እውነታዎች መካከል፡ ጥቂቶቹንም ቢኾን፡ ይኸው አሳውቃችኋለሁ።

፩ኛ፡ እነዚህ እውነታዎች፡ ዛሬ፡ በእኔ አንደበት እንዲገለጹ በማስፈለጉ ሲኾን፣ ይህም፡ አስፈላጊነት ለተፈጻሚነት የበቃው፡ በክፉ ሰዎች ዘንድ፡ በጽኑ የብረት መዝጊያ፡ ለዝንተ-ዓለም ተቆልፎበት የኖረውን ይህን፡ የዲያብሎስ ሓሰት፣ <u>የመለኮት ብቻ እንጂ፡</u> የፍጡር ኃይል፡ እስካኹን ከፍቶ፡ ከእስራቱ ሊያወጣው፣ ለፍጥረተ-ዓለሙ ሰዎችም አጋልጦ ሊከሥተው ሳይቻለው የቀረ መኾኑ ነው።

፪ኛ፡ "የእግዚአብሔር ቃል ነው!" በሚለው፡ በተለመደውና ኃይለኛ በኾነው፡ የሽፋን ዘዴያቸው በመጠቀም፡ "ወደፊት፡ ለእኛ ርስት ሊኾን ይገባል!" የሚሉትን ምድረ-ከነዓንን፣ የኋላ ኋላ፡ ለመውረስ ሲሉ፡ በሰብአዊው ብልጠታቸውና ረቂቅ ብልሃታቸው፡ ለዘረጉት፡ እኩይ ዕቅዳቸው አፈጻጸም ማመቻቸታቸው መኾኑ ነው፤

፫ኛ፡ በካምና በልጁ በከነዓን ላይ፡ ያን የመሰለ፡ አሠቃቂ ርግማንን ያስከተለው ድርጊት፡ በካም በኩል የተፈጸመው፡ ካም፡ ከኹለቱ ወንድሞቹ ቀድሞ፥ ወይም፡ ተራውን በመጠበቅ ተከትሎ፡ አባታቸው ኖኅ ወደነበረበት ድንኳን፡ በቅንነት መግባቱና በዚያ፡ በጎ ምግባሩ ምክንያት፡ ዕድሉ ኾኖ፣ አስቀድሞም ሳያውቅ፡ የአባቱን ራቁትነት ማየቱ፡ እንደታላቅ ጥፋት ተቆጥሮ፡ ያን የመሰለ ርግማንን ሊያስከትልበት የማይታሰብ፣ የማይገባም መኾኑ ነው።

፩ኛ፡ የቀሩት ኹለቱ ወንድሞቹም እኮ! የአባታቸውን ዕርቃን ለመሸፈን እንጂ፡ ላለማየት፣ ሸማ ዘርግተው፡ የኋሊት እየተራመዱ ሊኼዱ የቻሉት፣ ከዚህ የተነሣም፡ ከርግማኑ ነጻ፣ በምርቃቱም ባለጸጎች ለመኾን የቻሉት፡ አባታቸው ኖኅ የሚገኝበትን ኹኔታ፡ አስቀድሞ አይቶ፡ ወንድማቸው ካም ስለነገራቸው መኾኑ ነው።

፳ኛ፡ "የአባቱን፡ የኖኅን ዕርቃን አየ! ሳቀም!" የተባለው፣ በዚያን ጊዜም፡ በሕይወተ-ሥጋ ይኖር የነበረው፡ ካም ብቻ ሲኾን፣ ጨርሶ፡ በዚያ ሥፍራ ያልነበረው፣ በዚያ ድርጊትም ፈጽሞ ያልተካፈለው ከነአን፡ ዋናው የርግማኑ ተቀባይ መኾኑ ነው።

፫ኛ፡ ለመኾኑ፡ "ሰከረ!" የተባለው ኖኅ፡ **"ወኖኅሰ ረከበ ሞገሰ በቅድመ እግዚአብሔር፤ ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለኖኅ፤ ወብእሲ ጻድቅ ውእቱ፤ ወፍጹም፤ ወእምልደቱ አሥመሮ ለእግዚአብሔር። ...ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ፡- 'ባእ አንተ፣ ወኵሉ ቤትከ ውስተ ታቦት፤ እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ፡ በቅድሜየ፣ በዛቲ ትውልድ።**

"በኃጢአቱ ሊጠፋ ከተዘጋጀው፡ ከቀረው የዓለሙ ኅብረተ-ሰብ፡ ኖኅ ብቻ፡ ከነቤተሰቡ፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ሙገሳን [ባለሟልነትን] አገኘ፤ የኖኅ ተፈጥሮም፡ እንዲህ ነው፡- ከመወለዱ አንሥቶ፡ እግዚአብሔርን ያስደሰተ፣ እውነተኛና ፍጹም ሰው ነው። ...እግዚአብሔርም፡ ኖኅን፡ እንዲህ አለው፡- 'አንተ፣ መላውን ቤተሰብህን ይዘህ፡ የእኔን ቃል አምነህ ወደሠራኸው መርከብ ግባ! በዚህ ትውልድ መካከል፡ አንተን ብቻ፡ በፊቴ፡ እውነተኛ ኾነህ አግኝቼሃለሁና።" ተብሎ፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ የተነገረለትና የተጻፈለት፣ አካኼዱንም፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ፡ ከዚያ የጥፋት ውኃ፡ ራሱንና ቤተሰቡን ያዳነ፣ ፍጹም ጨዋ ሰው መኾኑ፡ በእርግጥ ይታወቃል።

እንዲህ የታወቀ ኾኖ፣ ነገር ግን፡ ከመጠን በላይ ጠጥቶ ሰክሮ፣ ራሱን እስኪስትና ልብሱን ጥሎ ራቁቱን እስከመኾን የደረሰ ከኾነ፣ በዚያን ጊዜ፡ በራሱና በአካባቢው የኾነውን ኹሉ፡ ፈጽሞ ሊያስተውል የማይችል ስለኾነ፡ *"ኖኅም፡ ከወይን ጠጁ ሰካር በነቃ ጊዜ፡ ታናሹ ልጁ "ከነአን" ያደረገበትን ኹሉ ዐወቀ።"* የሚለው ዐረፍተ-ነገር፡ ሓሰት መኾኑ ነው። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፮፥ ፰-፱፤ ፯፥ ፩።)

፯ኛ፡ ደግሞስ፡ የእኛን የፈጣሪያቸውን ሕያው ቃል ባለመከተላቸው፡ በራሳቸው ላይ የከፉትን፣ የኃጢአትንና የሞትን ፍዳ ካመጡት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከእነዚሁ የክፉዎቹ አይሁድ የኦሪት መጽሓፋቸው ድረስ፡ <u>ራቁትነት፡</u> በእየራሳቸው ላይ፡ እንደኀፍረት፥ እንደነውርና እንደኃጢአት እንዲቆጠር አደረጉት እንጂ፡ የእኛ የእግዚአብሔር የኾነውን የጸጋ ልብስ በተጐናጸፉት፣ ከፍጹሙ የቅድስና ብቅዓት ከመድረሳቸው የተነሣም፡ ከጥፋት ውኃ ለመዳን በቻሉት፡ በኖኅና በሚስቱ፣ በካምና በወንድሞቹ፥ በሚስቶቻቸውም ዘንድ፡ ራቁትነት፡ ኀፍረት፥ ነውርና ኃጢአት ኾኖ፡ ካምን፡ ያን ለመሰለ ርግማን የሚዳርገው አለመኾኑ ነው።

# የኖኅ እና የካም እውነተኛ ማንነት።

አዎን! ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እነዚህ ጥቂት እውነታዎች፡ በመለኮት አንደበት፡ እንዲህ እንዲነገር ያስፈለገው፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም። እስኪ በማስተዋል ተመልከቱት! ለመኾኑ፡ ከሰዎች ተራ ወሬ ወራዳነት ደረጃ ለማያልፈው፡ ለዚህ፡ ሓሳዊና መሠሪ የፈጠራ ታሪክ፡ ሰለባዎች የኾኑት "ኖኅ"፣ ይልቁንም፡ ገና ሳይፀነስ፣ ያለፍዳው የተኰነነውን፡ ከነዓንን፡ የኋላ-ኋላ የወለደው፡ ኹለተኛ ልጁ "ካም"፣ እኒህ፡ ኹለት፡ የቀደሙ፡ ደጋጎችና ንጹሖች፣ ጻድቆችና ቅዱሶች ሰብአውያን ፍጡሮቻችን እነማን ናቸው?

ካምን የወለደው ኖኅ እና ከነዓንን የወለደው ካም እኮ! እንደአያት ቅድመ-አያቶቻቸው፡ እንደሄኖክ፥ ከዚያም በመለስ፡ ኖኅ፡ ሚስቱን፡ ሓይከልን፣ ካምም፡ ወንድሞቹን፡ ሴምንና ያፌትን፣ ሚስቶቻቸውንም ኹሉ፡ ከራሱ ሚስት፡ ከከነዓን እናት ጋር ዐብረው በመኾን፡ **የህልውናና የሕይወት አካኼዳቸውን፡** በእውነተኛውና በመንፈስ-ቅዱሳዊ አምልኮታቸው፡ ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጋቸው፣ ለፍጹሙ የብቅዓት ማዕርግ የደረሱ አይደሉምን? አዎን! በእርግጥ፡ ለዚያ፡ ለፍጹሙ የብቅዓት ማዕርግ የደረሱ፡ **ጻድቃን** [እውነተኞች ሰዎች] ናቸው።

ታዲያ! እንዲህ ስለኾነ አይደለምወይ፡ "የሰው ልጆች" የተባሉት፡ የቃኤሎች ዘር የኾነው፡ ሌላው፥ መላው፥ የቀረው፡ የፍጥረት ወገን፡ በሰይጣናዊነቱ፡ እኛን ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ትቶ፡ እንደቀደሙት ወላጆቹ፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ በእንቢተኝነት፡ እባቡን ዲያብሎስን በመከተሉ፣ በዚህ ክህደቱና ዓመፁ፥ የአምልኮ አመንዝራነቱና ክፋቱ ምክንያት፡ ጽዋው ሞልቶ የፈሰሰው ኃጢአቱ ባመጣበት የጥፋት ውኃ፡ ከምድር ገጽ፡ ፈጽሞ የተደመሰሰው? አዎን! በእኛ በፈጣሪው ላይ ያመፀው፡ ያ፡ የሰዎች ትውልድ፡ በጥፋት ውኃ፡ ከምድር ገጽ፡ ፈጽሞ የተደመሰሰው፡ ጽዋው ሞልቶ በፈሰሰው ኃጢአቱ ምክንያት መኾኑ፡ እርግጥ ነው።

ኃጢአተኛው የፍጥረት ወገን በሙሉ፡ እንዲህ ሲደመሰስ፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" የተባሉት አቤሎች፡ ኖኅና ሚስቱ ሓይከል፣ ከልጆቻቸው፡ ከሴምና ከያፌት፣ ከሚስቶቻቸውም፣ ካምም፡ ከነዓንን ከወለደችለት ሚስቱ ጋር፣ እነርሱ ብቻ ከጥፋቱ ውኃ ሊተርፉ ያቻሉት ደግሞ፡ <u>የህልውናና የሕይወት አካኼዳቸውን፡ እንደቅድመ-አያታቸው፡ እንደሄኖክ፡ ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓት ጋር በማድረጋቸው፣ በዚህ ብቅዓታቸው የተነሣ መኾኑ፡</u> አዎን! እርግጥ፡ ነው።

ታዲያ! በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው፡ እውነተኛነትና ፍጹምነት፡ በእኛ ዘንድ፡ ይህን የመሰለው ታዋቂ ብቅዓት ያላቸውና ይህን የመሰለ ማንነታቸውን ያሳዩት፡<u>ኖኅ</u> እና <u>ካም</u> እኮ ናቸው፡ ገና፡ ካልተፀነሰው ልጅና የልጅ-ልጃቸው፡ ከከነዓን ጋር፡ ለዚያ ሓሳዊ የስካርና የዕርቃን ውርደት፣ ለዚያ ሓሳዊ ርግማንም፡ በከንቱ የተዳረጉት! ይህ ምትሓታዊና ሰይጣናዊ አስተሳሰብና አድራጎት አያስገርማችሁም? አዎን! ሊያስገርማችሁ ይገባል።

ልጄን ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ሰቅለው የገደሉት፡ እነዚህ፡ የዚህ ክፉ ደባ አመንጪዎችና ባለቤቶች የኾኑት "አይሁድ" የሚባሉት፡ የዲያብሎስ ልጆች፡ ለሥጋዊና ምድራዊ ጥቅማቸው ብቻ ሲሉ፡ እንዲህ፡ በጻድቆቹና በደጋጎቹ ልጆቻችን፡ በወንድ ወላጅዬው፡ በኖኅ፣ በወንድ ልጅዬውም፡ በካም ላይ፡ ሊያደርሱ የሞከሩት መሠሪ ጥቃታቸው፡ በዚህ፡ አሳፋሪ ማዋረጃቸውና ሓሳዊ ርግማናቸው ብቻ የተወሰነ መሰላችሁን? አይደለም፤ በእኛ በእግዚአብሔር ፊት፡ ፍጹም እውነተኛና የበቃ ኾኖ በመገኘቱ፡ የሰውን ዘር፡ ከፍጥረታዊ ህልውናው፡ ፈጽሞ ሊደመሰስ ከደረሰበት፡ ከመጨረሻው የጥፋት ጽንፍ አትርፎ ያዳነውን ኖኅን የሚያህለውን ታላቅ፡ አምላካዊ ሰው፡ ለዚያ የስካር ውርደት መዳረጋቸው ሳያንሳቸውና ሳይበቃቸው፡ በመሰል ደግ ልጁ፡ በካም ላይ ደግሞ፡ የወረወሩት፡ አቍማይ ብቻ ሳይኾን፡ እጅግ አሠቃቂ ገዳይ የኾነ መርዛማ ጦር፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ብትሰሙት፥ ወይም፡ በገዛ ዓይናችሁ ብትመለከቱት፡ ለማነኛችሁም፡ ለማመን የሚያስቸግራችሁ ሊኾን እንደሚችል፡ በቀላሉ ትገነዘቡታላችሁ።

ይኸውም፡ በየራሳቸው ሰይጣናዊ አእምሮ፡ ታስቦ የተነገረና የተደረገ፣ የሚነገርና የሚደረግ ካልኾነ በቀር፡ እንኳንስ፡ በእኔ መለኮታዊ አንደበት ሊነገር ቀርቶ፡ በማንም ሕያው ፍጡር ዘንድ ሊሰማ የማይገባውን፡ ከዚህ ሓሰተኛ ርግማናቸው ይልቅ፡ በብዙ መልኩና መጠኑ፡ በእጅጉ የባሰ ጸያፍ የኾነ ነውርን፡ "ታልሙድ" በተባለው መጽሓፋቸው ውስጥ ጽፈውት፡ ለይፋ ምንባብነት ክፍት ኾኖ ታገኙታላችሁና፡ እዚያ ተመልከቱት! እዚያም፡ ካም፡ እንደውሻ ታይቶ፡ የውሻን ግብር ሲፈጽም እንዲታይ የተደረገበትን የርኵሰት ውንጀላ ታገኙታላችሁ። ከዚያ በኋላ፡ የየግል ፍርዳችሁን፡ እዚያው፡ በየኅሊናችሁ ስጡ!

ሓሳዊው የኖኅ ርግማን፡ ወላፈኑ እንኳ፡ በራሱ፡ በካምና በልጁ በከነዓን ላይ ቀርቶ፡ በልጅ ልጆቻቸው ላይ፡ ያልደረሰባቸው ቢኾንም፣ ነገር ግን፡ እስከዛሬ ያሉት ዘር-ማንዘሮቻቸው የኾኑት፥ በዓለሙ ኅብረተ-ሰብም ዘንድ፡ "ጥቁሮች" የሚባሉት ካማውያን ኹሉ፡ ይህንኑ፡ ሓሳዊዉን እርግማን፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር እንደተሰጠ በመቍጠር፡ "የእኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው!" ብለው፡ በእየራሳቸውና በጋራ ጭምር፡ በሃይማኖት ተቀብለውት፣ በምግባርም አጽንተውት፡ በየዘመናቱ ትውልዳቸው፡ እንዴት፡ እንዲህ፡ በ<u>ጽኑ ጠንቁ</u> እየተዋረዱበትና እየተሠቃዩበት እንዲኖሩበት እንደተዳረጉ፡ ይኸው፡ ፍጥረተ-ዓለሙ፡ በሙሉ፡ በገሃድ ስለሚያየው፡ ኹሉ ያውቀዋል።

ታዲያ! ይህ ኹሉ ጥቃትና ግፍ፡ እስካኹን፡ እንዴት፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" ብላችሁ በስሜ በምትጠሩ በእናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሳይቀር፡ በሃይማኖት፡ ተቀባይነትን አግኝቶ፣ በምግባርም፡ ጸንቶ፡ እንዴት፡ እንዲህ ሲደርስና ሲፈጸም ኖረ? አኹንም እንኳ፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ፡ በበለጠ ተጠናክሮ፡ እንዴት እየቀጠለ ሊኼድ ቻለ?

አያችሁ! መልሱን፡ እናንተ ራሳችሁ ዐውቃችሁት ልትሰጡ ስትችሉና ሲገባችሁ፣ እርሱንም፡ በይፋ ተናግራችሁ፡ በተግባር ላይ ልታውሉት ሲገባችሁ፡ ይህን ተልእኳችሁን፡ እናንተ እንኳ፡ ሳትፈጽሙት በመቅረታችሁ፡ አያችሁ፡ እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምና ልጇ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እኛው ራሳችን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሳችን አማካይነት፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** በአካል መጥተን፡ በዚህ መለኮታዊ ዐዋጃችን እንድንገልጠውና እንድናጋልጠው አስፈላጊ ኾነ!

ይህም እውነታ አረጋግጦ የሚያሳያችሁ፡ ግዙፍ ኹኔታ አለ፤ ይኸውም፡ በአኹኑ የፍጻሜ ዘመን፡ በእኛ ምሥዋዐ-መድኃኒትነትና ቤዛ-መስቀለ-ሰላምነት፡ ለዘለዓለም ድል የኾነው ዲያብሎስ፡ በመጨረሻ፡ ከምድር፡ ከመወገዱ በፊት፡ ለእግዚአብሔራዊው የፍትሕ-ርትዕ ምዕራፍ መገለጥ፡ ለጥቂት ዘመን፡ ከእስራቱ እንዲፈታ ባደረግንበት፡ በዚህ ጊዜ፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ **"ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ-ኖኅ፡ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ-ዕጓለ እመሕያው!** በኖኅ ዘመን እንደኾነው ኹሉ፣ የማርያም ልጅ ዳግም-ምጽአቱም፡ እንዲሁ ይኾናል!" ካለው ኹኔታ፡ በባሰ መልክና ይዘት በሚገኘው፡ በመላው የዓለሙ ኅብረተ-ሰብ ላይ፡ ይኸው ዲያብሎስ፡ የቱን ያህል ሰፍኖ፡ እየገዛ እንዳለ ነው። (ማቴ. ፳፬፥ ፴፯-፴፱።)

ሊቀጥል የማይቻለውና ሊወገድ የሚገባው፡ ይህ፡ የዲያብሎስ የክፋት ምስፍና [አገዛዝ]፡ ጊዜው ስላበቃ፡ ይህ መለኮታዊ ዐዋጅ፡ በእኔ ቃል እንዲነገር፡ አስፈላጊ የኾነው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን ልትገነዘቡት ይገባል።

በተግባር ፍሬያቸው፡ የእኛ የእግዚአብሔር ሥራ የኾነውን፡ የተፈጥሮ ሥርዓት በማቃወስ፡ የዲያብሎስ አገልጋዮች መኾናቸውን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ አረጋግጠው ያሳወቁት፡ በቀዳሚነት፦ አሪታውያኑ የአይሁድ ካህናትና ሊቃነ-ካህናት፡ ከዚያም፡ የእነርሱን ፈለግ በመከተል፡ ሠርገው የገቡት፡ ኦርቶክሳውያኑ የግብፅ መነኮሳትና ጳጳሳት፡ በኢትዮጵያ ልጆቻችን ላይ ባመጡባቸው፡ የረዥም ዘመናት ጠንቀኛ ተፅዕኖ፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ከእኛ ከፈጣሪያቸውና ከአምላካቸው እግዚአብሔር ያገኙትን፣ ሲገለገሉበትና ሲያገለግሉበትም የኖሩትን፡ የተቀደሰ የሕይወት ሥርዓት ኹሉ፡ እንዴት አድርገው እንዳማሰኑባቸው፣ ለባዕዳኑ የአምልኮ ይትበሃላቸውም እንዴት አድርገው ለተገዢነት እንደዳረጓቸውን የሚያረጋግጡ ኹኔታዎችን፡ ከዚህ ቀጥዬ፡ እንደጀመርሁት፡ በክፍል፣ በክፍል አስደምጣችኋለሁ።

## ክፍል ኹለት።

## እግዚአብሔር፡ በአባትነቱ እና በእናትነቱ፣ በአዳም እና በሔዋን ተፈጥሮም፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ቅድስናን ያቀዳጀውን፡ ሥርዓተ-ጋብቻንና ሩካቤውን፡ ሰይጣናዊ በማስመሰል፡ ሊያረክስ የሞከረ፡ "ገድለ-አዳም" የሚባለውን ድርሳን በሚመለከት።

የዚህን አሳፋሪና አሳዛኝ ነገረ-ሓተታ፡ በእኔ አንደበት፡ ከመግለጼ በፊት፡ የቀደሙትን፡ የኦሪታውያኑን አይሁድ ካህናትንና ሊቃነ-ካህናትን፣ እንዲሁም፡ የኋለኞቹን፡ የኦርቶክሳውያኑን ግብፃውያን መነኮሳትንና ጳጳሳትን የመሰሉት፡ አኹንም፡ የእኛ የእግዚአብሔር ቃል እንደኾነ አስመስለው፡ የምንነቱ ዝርዝር፡ ቀደም ብሎ በተገለጸው፡ "ገድለ አዳም" የሚለውን ርእስ በሰጡት ድርሰታቸው ውስጥ፡ ከገጽ ፺፫-፺፬ ጽፈው የሚያስነብቡትን፡ እንዲህ የሚለውን ሓሳዊ ቃላቸውን፡ እስኪ በቅድሚያ ስሙት!

*"አዳም፡ ከገነት ከወጣ፡ መቶ አርባ ኹለት ቀን ተፈጸመ። በነጋ ጊዜም፡ አዳምና ሔዋን፡ ከቤታቸው ወጡ። ከቤት፡ ወደስንዴአቸው ቦታ፡ ወደምዕራብ ጫፍ ወረዱ። እንደልማዳቸውም፡ በዛፍ ሥር ተጠለሉ። ብዙ አራዊት መጥተው ከበቧቸው።*

*"ሰይጣንም፡ በክፋቱ፡ ይህን ያደርግ ነበር። አዳምን፡ በግቢ* [በጋብቻ] */በግብረ-ሥጋ ግንኙነት/ ምክንያት፡ ድል እስኪነሣው ድረስ።*

*"ከዚህ በኋላ፡ የመልካም ጠላት ሰይጣን፡ መልአክ መሰለ። በእርሱ አምሳልም፡ ሌሎች ኹለት ነበሩ። ለአዳም፡ ወርቅ፣ ዕጣን እና ከርቤን እንዳመጡለት መላእክት፡ ሦስት ነበሩ። በአዳምና በሔዋን ፊት አለፉ። እነርሱም፡ በዛፍ ሥር ነበሩ። ሽንገላን በተመላ ጥሩ ነገር፡ ከአዳምና ከሔዋን ጋር፡ እጅ ተነሣሱ። አዳምም፡ ፊታቸውን፣ መልካም ነገራቸውንም በተመለከተ ጊዜ፡ ቁሞ ተቀበላቸው። ወደሔዋንም አመጣቸው። ኹሉም ተቀመጡ። የአዳም ልቡናም፡ ደስተኛ ነበር።*

*"እርሱ /አዳም/፡ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ያመጡለት መላእክት እንደኾኑ፡ በልቡ አሰበ። እነዚያ መላእክት፡ አስቀድሞ፡ ወደአዳም በመጡ ጊዜም፡ ከእነርሱ የተነሣ፡ ዕረፍት፣ ደስታ፡ በእርሱ ላይ ነበር። መልካም የኾኑ ምልክቶችን ይሰጡት ዘንድ እንደመጡ አሰቧልና። ሰይጣን እንደኾነም አላወቀም። ስለዚህም፤ በደስታ ተቀብሎ፡ ከእነርሱ ጋር ተቀመጠ።*

"ከእነርሱ፡ ታላቁ ሰይጣንም፡ እንዲህ አለ፦ 'አዳም ሆይ! ፈጽሞ ደስ ይበልህ! እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ አንዲት ነገርን እነግርህ ዘንድ፡ ወደአንተ ልኮናልና፤' አለው።

"አዳምም፦ 'ምንድን ነው?' አለ።

"ሰይጣንም፦ 'ነገሩ /ቃሉ/ ቀላል ነው። እርሱም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ካልሰማህ፡ እኛ ወደእግዚአብሔር እንመለሳለን። ቃላችንን እንዳልተቀበልህም እንነግረዋለን።' አለው።

"ዳግመኛም ሰይጣን፦ 'አዳም ሆይ! ከእኛ የተነሣ፡ አትፍራ! መንቀጥቀጥም አይድረስብህ! አታውቀንምን?' አለው።

"አዳምም፦ 'አላውቃችሁም።' አላቸው።

"ሰይጣንም፦ 'እኔ፡ ወርቅን፡ እስከቤትህ ተሸክሜ ያመጣሁልህ፣ ይህ ኹለተኛው ደግሞ፡ ዕጣን፣ ይህ ሦስተኛው ደግሞ፡ ከርቤን ያመጣልህ ነው። ከተራራው፡ እስከቤትህ የተሸሙህ ናቸው፤' አለው። 'እስከቤት ያደረሷችሁን ጓደኞቻችንን ግን፡ እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር አልላካቸውም፤ እናንተ ትጠቀማላችሁና!' አላቸው።

"አዳምም፡ ይህን ቃል፡ ከእነርሱ በሰማ ጊዜ፡ አመናቸው። 'እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ተናገሩ! እኔም፡ እቀበለዋለሁ፤' አላቸው።

"ሰይጣንም፦ 'እንደምትቀበለው ማልልኝ! ቃል-ኪዳንም ግባልኝ!' አለው።

"አዳምም፦ 'እኔ፡ መሓላ እና ቃል-ኪዳን አላውቅም ፤' አለው።

"ሰይጣንም፦ 'እጅህን አውጣት፤ በእጄ ላይም አስቀምጣት! ‹የእግዚአብሔር እውነት፡ ሕያው ኾኖ የሚኖር፣ ከአርያም፡ ወደሰማይ ያረገ፣ መሬትን፡ በውኆች ላይ ያጸና እና ከአራቱ ባሕርያት የፈጠረኝ፡ እኔ፡ ቃል-ኪዳኔን አላረክስም፤ ቃሌንም አልለውጥም፤ /አላቆሽሽም/' በል!› አለው።

"አዳምም፡ እንዲሁ ማለ።

"ሰይጣንም፦ 'እነሆ! አንተ፡ ዘመን አለህ። ከገነት ከወጣህ ጀምሮ፡ ፈጽሞ ክፉን አታውቅም፤ እግዚአብሔር፡ ከጎንህ የወጣች ሔዋንን፡ ትወስዳት ዘንድ፣ የምትጽናናበት ልጅ ለመውለድም፡ ታገባት ዘንድ አዝዟል፤ ችግርም፣ ኃዘንም፡ ከአንተ ዘንድ ይርቃል። ይህ ሥራም፡ ከባድ አይደለም፤ መሰናክልም አይኾንብህም፤' አለው።

"አዳምም፡ ይህን፡ ከሰይጣን በሰማ ጊዜ፡ ስለመሓላው፡ ከባድ ኃዘንን አዘነ። አዳምም፡ ሰይጣንን አለው፦ 'እኔ፡ በዕድሜዬ፡ በሥጋዬ፡ እንዴት እዘሙታለሁ!? /እበድላለሁ!?/ ተቸግሬ፡ ከመሓላዬ ብመለስ፡ እግዚአብሔር ያጠፋኛል። ከምድር ገጽም ይደመስሰኛል። እኔ፡ ቀድሞ፡ ከዕፀ-በለስ በበላሁ ጊዜ፡ ከገነት፡ ወደዚች ኃላፊት ምድር አውጥቶኛልና። በሌላም በኩል፡ በእኔ ላይ ሞትን አመጣ፤ ዳግመኛም፡ ይህን ካደረግሁ፡ ሕይወቴን /ነፍሴን/፡ ከዚች ምድር ይወስዳል፤ ወደሲኦልም ያወርደኛል፤ እጅግም ያሠቃየኛል። የምትለኝን ይህን ቃል፡ እግዚአብሔር አልነገረኝም።

"እናንተም፡ የእግዚአብሔር መላእክት አይደላችሁም። ከእርሱ፡ ወደእኔ የተላካችሁም አይደላችሁም፤ እናንተ ሰይጣናት ናችሁ። በምትሓትም፡ መላእክትን መሰላችሁብኝ እንጂ። ከእኔ ወግዱ! እግዚአብሔር ይርገማችሁ!'

"ሰይጣናትም፡ ከአዳም ፊት ሸሹ። አዳምና ሔዋን ተነሥተው፡ ወደቤታቸው ተመለሱ። ወደውስጥም ገቡ።

"አዳምም፡ ሔዋንን፡- 'የማደርገውን ታያለሽን? አትናገሪምን? በታላላቅ ሰዎቹ ስለመማሌ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ይቅርታን አጣሁ። እጄንም፡ ዳግመኛ፡ በሰይጣን እጅ ላይ አደርጋለሁ።' አላት።

"ሔዋንም፡ አዳም ከነገራት የተነሣ፡ ዝም አለች።

"አዳምም ተነሥቶ፡ እጁን፡ ወደእግዚአብሔር ዘረጋ። ይቅር ይለው ዘንድ፤ ከእርሱ፡ ይቅርታን ፈልጓልና። ያደረገውን፡ ይቅር ይለው ዘንድም፡ ያለቅስ ነበር። አዳምም፡ እንዲሁ፡ ለጸሎት ቆሞ ነበር። ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት ያህል፡ እጁን በመዘርጋት፡ ከረኀቡ፤ ከጽሙ የተነሣ፤ በምድር እስከሚወድቅ ድረስም፡ አልበላም፤ አልጠጣም።

"እግዚአብሔርም፡ ቃሉን፡ ወደአዳም ላከ፤ ከወደቀበትም አነሣው። 'አዳም ሆይ! በሰማዮች ለምን ማልህ? ኹለተኛስ፡ ከሰይጣን ጋር፡ ለምን ተማማልህ?' አለው።

"አዳምም አለቀሰ። 'አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ይህን፡ ሳላውቅ አድርጌዋለሁና፡ ይቅር በለኝ!' አለ። 'የእግዚአብሔር መላእክት እንደኾኑ አምኜ ነበርና!' አለ።

"ይቅርም አለው። 'ከሰይጣን ተጠንቀቅ!' አለው። እግዚአብሔርም፡ ከአዳም ጋር ንግግሩን ፈጸመ።

"አዳምም፡ ልቡናው ተጽናና። ሔዋንንም ወሰዳት። እንደልማዳቸው፡ ለሥጋቸው፡ ምግብ ያዘጋጁ ዘንድ፡ ከቤት ወጡ።

"ከዚያች ሰዓት ጀምሮ፡ አዳም፡ ሔዋንን፡ በሩካቤ-ሥጋ ያውቃት ዘንድ፡ ሕሊናው ይፈታተነው ነበር። ይህን ያደርግ ዘንድ ይፈራ ነበር። እግዚአብሔር እንዳይቆጣው።

"አዳም እና ሔዋንም፡ ወደውኃ ምንጭ ኼዱ። በሚደሰቱ ሰዎች አምሳልም፡ በዚያ ተቀመጡ።

"ሰይጣንም፡ በእነርሱ ቀና። እርሱ፡ ከሰራዊቱ፡ ዐሥሩ፡ እንደእነርሱ ያለ ደም-ግባት የሌለ ደናግልን መሰሉ። ከውኃውም፡ ወደአዳምና ወደሔዋን ወጣ። እርስ-በርሳቸውም፡ 'ዓለምን የመላች፡ የአዳምና ሔዋንን መልክ ገጽ እንመልከት! መልካቸው፡ ከእኛ የተለየ፤ እነርሱም፡ ከእኛ ያማሩ ናቸውና!' ተባባሉ።

"አዳም እና ሔዋንም፡ ወደጫፍ ደረሱ። እጅም ነሷቸው፡ ከእነርሱ የተነሣም፡ እያደነቁ ቀሩ።

*አዳምና ሔዋንም፡ ከደም-ግባታቸው የተነሣ በማድነቅ፡ ወደእነርሱ ተመለከቱ። 'እኛ ከምንኖርባት ምድር ታች፡ መልካም ፍጥረት ያለባት፡ ሌላ ዓለም አለችን?' አሉ። እኒህ ደናግልም፡ ለአዳምና ለሔዋን፡- 'እውነት ነው፤ ፍጥረታችንም፡ ብዙ ነው፤' አሉ።*

*"አዳምም፡- 'የምትባዙት፡ በምንድን ነው?' አላቸው።*

*"'እኛ፡ የሚያገቡን ባሎች አሉን። ከእነርሱም፡ እንፀንሳለን። ልጅ እንወልዳለን። ልጆችም ያድጋሉ። በዚህም እንባዛለን። አዳም ሆይ! የማታምነን ከኾነ፡ እኛ፡ ባሎቻችንን፣ ልጆቻችንን እናሳይሃለን፤' አሉት። ልጆቻቸውን፣ ባሎቻቸውን እንደሚጠሩም፡ በባሕር ላይ ነበሩ። ከባሕሩም፡ ሰዎች እና ሕፃናት ወጡ። ከእነርሱ፡ እያንዳንዱ፣ ኹሉም፡ ወደሚስቱ፣ ወደልጆቹም ይደርስ ነበር።*

*"አዳም እና ሔዋንም፡ ባዩዋቸው ጊዜ ኼዱ። ከእነርሱ የተነሣም አደነቁ። እነርሱም፡ አዳምን እና ሔዋንን፡- 'እነሆ፡ ባሎቻችንን፣ ልጆቻችንን ተመለከታችሁ፤ ፅንስ ሲኾን ግን፡ አታውቁም። አዳም ሆይ! ሥራውን መጀመርን፡ አንተ፡ በሔዋን ላይ፡ እንዴት እንደምታደርግ እናሳይሃለን።' ብለው፡ አንዱም፣ ሌላውም፡ በአዳም ፊት፡ ክፉ ማድረግን /ሩካቤ-ሥጋ መፈጸምን/ ጀመረ።*

*"ከዚህ በኋላ፡ አዳምን፡- 'አንተም፡ በሔዋን ላይ፡ እንዲህ አድርግ!' አሉት። 'ልጅ ትወልዳለህ፤ ዘር ትተካለህ፤ ትባዛለህም።' አሉት። ሰይጣን ይሸነግለው ዘንድም፡ በአዳም ፊት፡ ይህን ያደርግ ነበር።"*

አኹን ደግሞ፡ የቅዱሳት መጻሕፍታችሁ መጀመሪያ በኾነው፡ ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥረት] በሚለው ክፍል፡ በቀዳማዊው ምዕራፍ፣ ከቍጥር ፳፮ እስከ፳፰፣ በሦስተኛው ምዕራፍ፣ በቍጥር ፳፱ እና በአምስተኛው ምዕራፍ፥ ከቍጥር ፩ እስከ፪ ድረስ ላይ የተጻፈውን፡ የእኛ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ እውነተኛውንና ትክክለኛውን ቃል፡ እስኪ ስሙት! እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው፡-

**"ወይቤ እግዚአብሔር፡- 'ንግበር ሰብአ፡ በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ፣ ከመ ይኰንን ዓሣተ-ባሕር፣ ወአራዊተ-ምድር፣ ወአዕዋፈ-ሰማይ፣ ወእንስሳሂ፣ ወኵሎ ምድረ፣ ወኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር።' ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በአምሳለ-እግዚአብሔር። ተባዕተ፥ ወአንስተ፡ ገብሮሙ። ወባረኮሙ እግዚአብሔር፤ ወይቤሎሙ፡- 'ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር! ወቅንይዋ! ወኰንንዎሙ፡ ለዓሣተ-ባሕር፣ ወለአራዊተ-ምድር፣ ወለአዕዋፈ-ሰማይ፣ ወለኵሉ እንስሳ፣ ወለኵሉ፡ዘይትሐወስ ዲበ ምድር።**

***"ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ፤ ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ።"***

***"ወበዕለት፡ አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም፡ በአምሳለ-እግዚአብሔር፡ ገብሮሙ፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ፤ ወባረኮሙ። ወሰመየ ስሞ፡ 'አዳም' በዕለት፡ እንተ ባቲ ፈጠሮሙ።"***

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'ሰውን፡ በአንዱ፡ በእግዚአብሔራዊው መልካችን፤ ደግሞም፡ በእግዚአብሔር አብ እና በእግዝእተብሔር እም አምሳያችን እንፍጠር! የባሕር ዓሦችንና የምድር አውሬዎችን፣ የሰማይ ወፎችንና እንስሶችንም፣ ምድርንም ኹሉ፣ በምድር ላይ የሚኖረውን ኹሉ ያስተዳድር ዘንድ።' ይህንም ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የሕያዋን-እናት-ልጅን [ሰውን]፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረ። እንደእግዚአብሔር አብ፡ ወንድ፣ እና፡ እንደእግዝእተብሔር እም፡ ሴት አደረጋቸው። 'ብዙ! ተባዙም! ምድርንም፡ ሙሏት! አቅኗትም! የባሕር ዓሦችንና የምድር አውሬዎችን፣ የሰማይ ወፎችንና እንስሶችንም ኹሉ፣ በምድር ላይ የሚኖረውን ኹሉ አስተዳድሯቸው!' ብሎም ባረካቸው።

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'እነሆ፡ አዳም፡ መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ፡ ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!"

"እግዚአብሔር አዳምን፡ በእግዚአብሔር አምሳል በፈጠረው ቀን፡ ወንድ እና ሴት አደረጋቸው። ባረካቸውም። በፈጠራቸው ቀን፡ 'አዳም' ብሎ ጠራው።" (ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] ፩፥ ፳፮-፳፰፤ ፫፥ ፳፪። ፭፥ ፩-፪።)

እንግዴህ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ አዳምን እና ሔዋንን፡ እንዲህ አድርገን፡ በእኛ እግዚአብሔራዊ ማንነትና ምንነት፡ ወንድ እና ሴት፣ ሚስት እና ባል፣ ወላጅ እና ወላጂት፣ ልጂት እና ልጅ፣ ወንድም እና እኅት፣ ንጽሕት እና ንጹሕ፣ ቡሩክ እና ቡርክት፣ ምልእት እና ምሉእ፣ ካህን እና ካህኒት፣ ልዕልት እና ልዑል፣ ብፁዕ እና ብፅዕት፣ ንግሥት እና ንጉሥ፣ ፍጹም እና ፍጽምት፣ ቅድስት እና ቅዱስ ለሚያሰኘው የመጨረሻ አምላካዊ ማዕርግ አብቅተን የፈጠርናቸው ናቸው።

እንዲህ አድርገን የፈጠርናቸው እነርሱ፣ ይህን መለኮታዊ ጸጋና በረከት፡ በገዛ ፈቃዳቸውና ምርጫቸው፡ ቢያማስኑት እንኳ፡ በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ምሥዋዐ-መድኃኒትነት እና በልጄ-በወዳጄ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰላመ-መስቀሉ ቤዛነት፡ ወደቀደመው ገነታዊ ሕልውናቸውና ዘለዓለማዊ ሕይወታቸው መልሰናቸዋል።

ታዲያ! "ይህ ጕድኣል!" በማይባል፡ በመንፈስ ቅዱሳዊው ዕውቀታችን አበልጽገን፡ ወደቀደመው ገነታዊ ሕልውናቸውና ዘለዓለማዊ ሕይወታቸው የመለስናቸው፡ አዳም እና ሔዋን፡ በየራሳቸው አእምሮ፡ ዐውቀውትና ፈቅደውት፥ ተፋቅረውና ተስማምተው፡ በገዛ ሥልጣናቸው ሊያደርጉት የሚቻላቸውን የተቀደሰውን የጋብቻቸውን ሩካቤ-ሥጋ መፈጸም እንዴት ያቅታቸዋል? ያዳግታቸዋልም? በደመ-ነፍስ ሕያዋን ኾነው የሚንቀሳቀሱት፡ እንስሳት፣ አራዊትና አዕዋፍ እንኳ፡ በተፈጥሮ ጠባይዓቸው ዐውቀው የሚፈጽሙት አይደለምን?

እኒህ፡ በፍጹሙ እግዚአብሔራዊው ዕውቀት የከበሩ ባል እና ሚስት፡ ምንም እንደማያውቁ ሕፃናን [ጎደሎዎች] ፍጡራን ተቆጥረው፡ እንዲህ፡ የሰይጣን እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ደካሞች እና መጫወቻዎች ኾነው መቅረባቸው፡ ምክንያቱ፡ ለምን እንደኾነ ለማወቅና ለመረዳት፡ ለእናንተ፣ ማስተዋሉ ስለጎደላችሁ፡ ቢያዳግታችሁም፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ሊሠወር አይቻልም።

ያም ምክንያት፡ በመለኮታዊው እና በትስብእታዊው ማንነታችንና ምንነታችን፣ ጥበባችንና ሥልጣናችን፡ ለሕያዉ ፍጥረታችን መልካም ሕይወት እና ዘለዓለማዊ ህልውና፡ በፍጹምነት የሠራነውንና በቋሚነት የመሠረትነውን፣ እኛም ለራሳችን ሠርተንበት፣ ፍጡሮቻችንም ተከትለው እንዲሠሩበት አድርገን፡ እየኖሩበት ያለውን ሥርዓተ-ጋብቻን፡ ከነሥነ-ምግባሩ ለማማሰን መኾኑን የሚያረጋግጠው እውነታ ነው። ይህም የጥፋት ድርጊት የሚካኼደው፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ የእኛን የሥነ-ፍጥረት ሥራ ኹሉ ለማደናቀፍና ለማቃወስ ብቻ ሳይኾን፣ ጨርሶ ለማፈራረስም ጭምር፡ በተቃዋሚነት ሲጥርና ሲግር በኖረው፣ አኹንም እየጣረና እየጋረ ባለው፡ በዲያብሎስ ሲኾን፣ ይኸው፡ የእርሱ፡ እኩይና መሠሪ ዓላማው፡ ከግብ ሊደርስለት የሚችል መስኣቸው፡ ሠራዊቱ ሰይጣናት፣ ከእነርሱም ጋር፡ የክፋቱና የጥፋቱ ዐባሪዎችና ተባባሪዎች የኾኑት የሰው ወገኖች፡ ያለ የሌለ፡ የመጨረሻ ኃይላቸውን፡ በተግባር ላይ ለማዋል መፈለጋቸው መኾኑ፡፡ በዚሁ ድርሳናቸው መጽሔትነት መረጋገጡ ሊታበል አይቻልም።

ይህንኑ ለማረጋገጥ፡ በዚሁ፡ በገድለ-አዳማዊው ድርሳናቸው ውስጥ የተሠነዘሩትን አንዳንዶቹን ኃይላተ-ቃላት እየጠቃቀሱ ማመልከት ይቻላል።

፩. እዚህ ላይ፡ በመሠረቱና በአጠቃላይ፡ ከኹሉ በማስቀደም፡ ሊቀርብና ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ አለ፤ ይኸውም፡ "በፍጡራን ኹሉ ዘንድ፡ የታወቀና የተለመደ፡ የተፈጥሮ ግዳጅ የኾነውን፡ ይህን የጋብቻና የሩካቤ-ሥጋን ነገር፡ እንደትልቅና ልዩ ጉዳይ አድርጎ ማንሣቱና ማቅረቡ፡ ቀድሞውኑ ለምን አስፈለገ?" የሚለው ነው። መልሱም፡ አጭርና ቀላል፣ ቀጥተኛም ነው፤ እርሱም፡ "ያው፡ እርሱኑ፡ <u>ጋብቻንና ሩካቤ-ሥጋውን በማዋረድና በማራከስ፣ ምንዝርስናን ለማሞጋገስና ለማነጋገሥ ስለተፈለገ፡</u> በእነርሱው በመነኮሳቱ፡ ተቀነባብሮ የተዘጋጀ መኾኑ፡ በደራሲዎቹ ማንነት፡ በቀላሉ ይታወቃል።" የሚል ይኾናል።

፪. *"ሰይጣን፡ በክፋቱ፡ አዳምን፡ በግቢ* [በጋብቻ] */በግብረ-ሥጋ ግንኙነት/ ምክንያት፡ ድል እስኪነሣው ድረስ።"* ተብሎ ስለተጻፈው:-

አዳምና ሔዋን፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር ተፈጥረውና ተጋብተው፡ በዚሁ ጋብቻቸው፡ ባልና ሚስት ኾነው፡ "ብዙ! ተባዙ!" ተብለው፡ በእኛ በፈጣሪያቸው የተባረኩበትን ጸጋ፡ ለፍሬ ለማብቃት፡ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ቢፈጽሙ፡ ምን ኃጢአት ኾኖባቸው ነው፡ ሰይጣን ድል ሊነሣቸው የሚቻለው? በእኛ በእግዚአብሔር ተሠርቶላቸውና ተቀድሶላቸው፣ ተባርኮላቸውና ተፈቅዶላቸው የፈጸሙት ጋብቻቸውና ሩካቤ-ሥጋቸው፡ "በሰይጣን ድል ከመኾን አደረሳቸው!" ለማለት የተፈለገው፡ የእኛ የእግዚአብሔር ሥርዓት የኾነውን ጋብቻን፣ ከእርሱም ጋር የተያያዘውን፣ ልጅ የሚያስገኘውን ሩካቤ-ሥጋን መፈጸም፡ ኃጢአት ስለኾነ፡ ይህ እግዚአብሔራዊው የጋብቻ ሥርዓታችንና ቅዱሱ የሩካቤ-ሥጋ ምግባሩ፡ ራሱ፡ በሰይጣን ድል የመነሣት መታወቂያ ምልክት መኾኑን አረጋግጦ ለማሳየትና ለማመልከት ነው።

ይህ ኹሉ የእጅ-አዙር ማመስጠርና መራቀቅ፣ ይህ ኹሉ ደባ፡ አዎን! ሴትነትንና ወንድነትን፣ እነርሱ የሚያስገኙትንም ጋብቻን፡ መርገም እና ርኵሰት፣ የጋብቻ ሩካቤ-ሥጋንም ሳይቀር፡ ነውርና ኃጢአት የሚያደርገውን ምንኵስናን ለማስከበርና ለማስወደድ፣ ለማስጸደቅም ነው።

፫. *"ሰይጣንም፡- 'እግዚአብሔር፡ ከጎንህ የወጣች ሔዋንን፡ ትወስዳት ዘንድ፣ የምትጽናናበት ልጅ ለመውለድም፡ ታገባት ዘንድ አዝዟል።'"* ተብሎ ስለተጻፈው:-

አዳምና ሔዋን፡ የዕውቀት ዛፍ ፍሬን በበሉ ጊዜ፡ "ከእኛ ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዝእተብሔር እም፡ እንደአንዳችን ኾናችሁ!" በተባሉበት፣ ፍጹሙን እግዚአብሔራዊ ብቅዓትንም ባገኙበት የዕውቀት ጸጋቸው፡ እኛ እግዚአብሔር፡ "ብዙ! ተባዙ!" ብለን የሰጠናቸውን፡ የህልውና መመሪያ ተከትለው፡ በወንድነት እና በሴትነት ጾታቸው መፈጸም የሚችሉት፡ በጋብቻቸው መኾኑን ማወቅ ተስኗቸው፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ለዚህ ትእዛዝ መድረስ፡ ሰይጣንን፡ መልእክተኛ አድርገን እንደሰደድን ኾኖ፡ በድርሳናቸው ውስጥ መጻፉ፡ ጸሓፊዎቹን መነኮሳት፡ በፍርድ ቀን፡ በብርቱ የሚያስጠይቃቸው ነው።

፬. *"አዳምም፡ ይህን፡ ከሰይጣን በሰማ ጊዜ፡ ስለመሓላው፡ ከባድ ኃዘንን አዘነ። ሰይጣንንም አለው:- 'እኔ፡ በዕድሜዬ፡ በሥጋዬ፡ እንዴት እዘሙታለሁ!? /እበድላለሁ!?/ 'አላቸው። ..."እግዚአብሔር ያጠፋኛል። ከምድር ገጽም ይደመስሰኛል። ዳግመኛም፡ ይህን ካደረግሁ፡ ሕይወቴን /ነፍሴን/፡ ከዚች ምድር ይወስዳል፣ ወደሲኦልም ያወርደኛል፣ እጅግም ያሠቃየኛል።"* ተብሎ ስለተጻፈው:-

እኛ እግዚአብሔር የሠራነውና የፈጸምነው፣ ከአዳም እና ሔዋን ጀምሮም፡ ሕያዋን ፍጡሮቻችን ኹሉ፡ የእኛን ፈለግ ተከትለው ይፈጽሙት ዘንድ፡ ለፍጥረት የህልውና ሥምረትና መልካም ውጤት፡ አሳምረንና ቀድሰን የሰጠነው ጋብቻ፡ እንዴት የዝሙት ማካኼጃ መድረክ እስከመኾን ደርሶ፡ እንዲህ በገሃድና በድፍረት ሊነቀፍና ሊዘለፍ ቻለ!? ወንድ እና ሴትም፡ በመጋባታቸው ብቻ፡ በከባድ የሚያዝኑ፣ በዚሁ ጋብቻቸው የሚፈጽሙትም የባልና ሚስት መኻታቸውና ሩካቤ-ሥጋቸው፡ እንደታላቅ ኃጢኣት ተቆጥሮባቸው፡ እንዴት የሚያስቀጣቸው ኾኑ!? እኛ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርም፡ እንደጨቃኞች ተቆጥረን፡ እኒያን ባልና ሚስት፡ በሞት የምንቀጣቸውና የምናጠፋቸው፣ ከምድር ገጽም የምንደመሥሳቸው፣ ወደሲኦልም አውርደን የምናሠቃያቸው ኾነን ተገኘን እኮ።

በተቀደሰው እውነተኛ ጋብቻ አንድ ኾነው፡ ልጆችን ወልደው፣ ለረዥም ዘመን፡ በፍቅርና በደስታ በሚኖሩ ባልና ሚስት መካከል፡ መነኮሳት፡ ይህን በመሰለ ሰይጣናዊ መልክና ይዘት ጣልቃ እየገቡ፡ ስንቱን ትዳር እንዳፈረሱ እናውቃለን። መነኮሳት ኹሉ፡ ስለዚሁ የጥፋት ድርጊታቸው፣ ደግሞም፡ ይኸው ድርጊታቸው፣ ጽሑፋቸውም፡ የቅዱሱ ጋብቻ ሥርዓት ሠሪዎቹና መሥራቾቹ፣ ፈጻሚዎቹና አስፈጻሚዎቹ የኾንነውን፡ እኛን እግዚአብሔርን፡ ራሳችንን፡ በቀጥታ መንቀፍና መዝለፍ፣ መወንጀልም በመኾኑ፡ መንፈስ-ቅዱስን እንደመስደብ አስቆጥሯቸውል። ከዚህ የተነሣም፡ በምድርም፣ በሰማይም፡ ስለማይሰረይላቸው፡ ስለዚሁ ኃጢኣታቸው፡ ነቃፊዎቹና ዘላፊዎቹ፡ ኹሉም፡ ፍርዳቸውን፡ በዚያ፡ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ይቀበላሉ።

፫. *"__አዳም፡ ስላደረገው፡ እግዚአብሔር ይቅር ይለው ዘንድ፤ ያለቅስ ነበር። ለጸሎት ቆሞ፡ ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት ያህል፡ እጁን በመዘርጋት፡ ከረኀቡ፣ ከጽሙ የተነሣ፣ በምድር እስከሚወድቅ ድረስም፡ አልበላም፤ አልጠጣም።__"* ተብሎ ስለተጻፈው:-

አዳም፡ በተቀደሰው የእኛ የእግዚአብሔሩ የጋብቻ ሥርዓታችን ያገባትን ሚስቱን ሔዋንን፡ በሩካቤ-ሥጋ፡ በአካል መገናኘቱ ቀርቶ፡ ገና ለመገናኘት፡ ማሰቡን እንኳ፡ እንደኃጢኣት እንዲቆጥረው፣ በዚህም፡ እኛን ፈጣሪውን፡ እንደበደለ፡ ቆጥሮ፡ ራሱን እንዲያስጨንቅ፣ ከዚያም አልፎ፡ ለአርባ ቀኖች ባካኼደው ጾምና ጸሎት ምክንያት ደክሞና ዝሎ፡ በመሬት ላይ እስከመውደቅ እንዲደርስ በማድረጋቸው፡ የዚህ፡ ልብ-ወለድ ድርሰት ጸሓፊዎች መነኮሳት፡ በሌሎቹ አዳምን እና ሔዋንን በመሰሉ ፍጡሮቻችን ላይ፡ ትልቁን በደል ፈጽመዋልና፣ እየፈጸሙም ናቸውና፡ በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል።

"ሰይጣን፡ በአዳም ላይ፡ ይህን አደረገ!" ብለው፡ መነኮሳት፡ ከራሳቸው ክፉ አእምሮ አንቅተው የጻፉትን፡ ይህን ኹሉ የሓሰት ቃል፡ እስከዛሬና ዛሬም ባሉት፡ በመላዎቹ ሰብአውያንና ሰብአውያት ፍጡሮቻችን ሰውነት ውስጥ አሳድረውት ያኖሩት ስለኾነ፡ ይኸው ጠንቀኛ ቃል፡ እነዚሁኑ ምስኪኖች ፍጡሮቻችንን ሲያሠቃይ የኖረውን ያህል፤ እነሆ፡ አኹንም፡ ይኸው እያሠቃያቸው ይገኛል።

ይህም፡ በአንድ እግዚአብሔር መልካችን፤ ከዚያም፡ የኹለትነት ምሳሌያችን በኾነው፡ በእግዚአብሔር አብ፡ የወንድነት ጾታ እና በእግዝእተብሔር እም የሴትነት ጾታ የፈጠርናቸው ሰዎች፡ እንደገና በጋብቻ አንድ ኾነው፡ መሰሎቻቸውን ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ሊያስገኙ ይችሉ ዘንድ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በፍጹሙ እና በኃያሉ መለኮታዊ ጥበባችን እና ሥልጣናችን፡ በወንዱ እና በሴቷ፡ በእያንዳንዳቸው ሰውነት ውስጥ፡ በሥነ-ፍጥረት ሥርዓት አርቅቀንና አስውበን፡ እንዲዘጋጅና እንዲፈልቅ ያደረግነው፡ የወንዱ ዘርና የሴቷ የወር አበባ፡ ከአሳባዊውና ከፍትወታዊው የፍቅር ስሜት ጋር፡ ከእኛው ከእግዚአብሔራዊው ባሕርያችን የተገኘ፡ መልካምና ንጹሕ፤ ቅዱስና ጽድቅ በመኾኑ፡ በዚሁ ኹኔታ ተይዞ፤ ተከብሮና ተወድዶም ሊሠራበት በተገባ ነበር።

የእኛ፡ የፈጣሪያችሁ እግዚአብሔራዊው እውነታ፡ ይህ ኾኖ ሣለ፥ ነገር ግን፡ ይኸው መልካምና ንጹሕ፤ ቅዱስና ጽድቅ የኾነው የወንዱ ዘርና የሴቷ የወር አበባ፡ እንደኃጢአትና እንደመርገም፥ እንደርኵሰትና እንደእከይ ተቆጥሮ፡ በዚያ ሓሰተኛ ድርሳናቸው ውስጥ፡ የሰይጣን መጫወቻና ማላገጫ ኾኖ እንደቀረበው፡ እንደአዳም ኹሉ፡ መላዎቹ፡ የሰዎች ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችን ኹሉ፤ እናንተ ጭምር፡ ይኸው በዚሁ ጠንቀኛ መርዝ፡ እየተሠቃያችሁ ትገኛላችሁ።

፯. *__"ከዚያች ሰዓት ጀምሮ፡ አዳም፡ ሔዋንን፡ በሩካቤ-ሥጋ ያውቃት ዘንድ፡ ሕሊናው ይፈታተነው ነበር። ይህን ያደርግ ዘንድ ይፈራ ነበር። እግዚአብሔር እንዳይቆጣው።__*

ተብሎ ስለተጻፈው፦

ለዚህኛውም አሳፋሪና መሠሪ የውሸት ቃላቸው፡ የሚሰጠው ተገቢ መልስ፡ እስካኹን ስትሰሙት ከቆየው፡ የተለየ አይኾንም።

እኛ እግዚአብሔር፡ "ምን ጥፋት አደረገ!? ምንስ በደለ!?" ብለን ነው፡ አዳምን የምንቆጣው? እኛ፡ እርሱን የምንቆጣበት፡ ምንም ምክንያት የለም። እርሱስ፡ "ምን ጥፋት አደረግሁ!? ምንስ በደልሁ!?" ብሎ ነው፡ እኛን የሚፈራው? እርሱም፡ እኛን የሚፈራበት፡ አንዳችም ምክንያት የለም። መንፈስ-ቅዱሳችን፡ የሰይጣን አገልጋዮች የኾኑትን መነኮሳት፡ ፊታቸውን ጸፍቶ፥ ጣቶቻቸውንም አስጠንቍሎ፡ በዚያ ድርሳናቸው ውስጥ፡ ይህን ቃላቸውን ያስጻፋቸው፡ አስተሳሰባቸውና አሠራራቸው፡ እንደዚያው እንደጌታቸውና አዛዦቻቸው፥ መሪያቸውና መምህራቸው፡ እንደዲያብሎስ ስለኾነ፤ የራሳቸውን እውነተኛ ማንነት ሊያጋልጣቸው፤ ውሳጣዊ ዓላማቸው የኾነውንም፡ ያንኑ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሥርዓት የኾነውን ጋብቻን በመፃረር፡ ለማራከስ ብቻ መኾኑን ሊከሥትባቸው ነው።

እንዲያ ካልኾነማ! ታዲያ! ለምንድር ነበር፡ አዳምን፡ "ባትበላ ይሻልሃል!" ብለን፡ እኛ እግዚአብሔር ካበረከትንለት ምክር ይልቅ፡ "የለም! መብላቱ ነው የሚሻለኝ!" ብሎ፡ ደጉንና ክፉውን፥ እውነቱንና ሓሰቱን፣ ሕይወቱንና ሞቱን፡ ለይታ ያሳወቀችውን፣ ከእኛ፡ እንደአንዳችን ለመኾን ያበቃችውንም፡ የዕውቀት ዛፍ ፍሬን፡ በገዛ ፍላጎቱና ምርጫው፡ እስከመብላት ያደረሰችውን፣ ምንጊዜም፡ የወደደውን ኹሉ ለማድረግ እንዲችል፡ እኛም፡ በመለኮታዊው ፈቃዳችንና ቸርነታችን፡ ፍጹሚን ነጻነት፡ ለዘለዓለም ላንነሣው፡ በጸጋ የሰጠነው!? ከዚህ የተነሣ፡ እኛም፡ እርሱን የምንቀጣበት፣ እርሱም፡ እኛን የሚፈራበት፡ አንዳችም ምክንያት የለም።

እነርሱኑ፡ አዳምን እና ሔዋንን፡ መጀመሪያ፡ "አዳም" በሚል ጾታ-አልባ ስም፡ በአንድነት ከፈጠርናቸው በኋላ፡ እንደገና፡ ወደአንድነት በሚመለሱበት ጋብቻ፡ ልጆችን በመውለድ እንዲባዙ ለማድረግ፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ በፍጹም እኩልነት፡ ከኹለት ከፈልናቸው። ታዲያ! እንዲህ፡ እኛው እግዚአብሔር የሠራነውን ሥርዓትና የሰጠነውን መመሪያ ተከትሎ ሊኖር የሚገባው አዳም፡ ሚስቱን ሔዋንን፡ በሩካቤ ሥጋ ለመገናኘት ቢፈልግ፡ እኛም፡ አበጀህ! መልካምም አደረግህ ብለን ደስ ይለናል፤ እርሱንም፡ ለወግ፣ ለማዕርግ በቃህልን!" ብለን፡ እንመርቀዋለን እንጂ፡ እንዴት እንቀጣዋለን?

እርሱም፡ አዳም፡ ፍጹም የሚወድዳትን ሚስቱን ሔዋንን፡ በፍጹም ፍቅር ዐቅፎ እየሳመ፣ እርሷም፡ ሔዋን፡ ፍጹም የምትወድደውን ባሏን አዳምን፡ በፍጹም ፍቅር ዐቅፋ እየሳመች፡ ኹለቱም፡ በመኻታቸው ላይ፡ ምንም ዓይነት እንከን በሌለበት፣ ምናልባትም እንከኑ ኖሮ ቢኾን እንኳ፡ ኋላ በፍጻሜ የሕይወት ዘመን፡ በእኔ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ-መድኃኒትነት እና በልጇ-በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የሰላመ-መስቀል ቤዛነት በተገኘው ንስሓ፡ እንዳልነበረ ኾኖ፡ ፈጽሞ ስለተወገደ፣ በዚያ ፍጹም ንጽሕናቸውና ቅድስናቸው፡ ሩካቤ-ሥጋቸውን፡ በፍጹም ሓሤትና ስባሔ መፈጸም ብቻ እንጂ፣ በዚያን ጊዜ፡ የምን የጎሊና ፈተናና መፈታተን ነው የሚኖረው? ይኼ ኹሉ፡ ፈጽሞ የለም። አይኖርምም። ኹሉም ዓይነት የክፋት እና የጥፋት፣ የኃጢኣት እና የሞት ቀንበር እና ጠንቅ፡ በእኛ በእግዚአብሔር፡ ከኹሉም ሕያው ፍጡራችን አካል ወልቆ እና ተመንጥቆ፡ ወደኀበ-አልቦነቱ [ወደአለመኖርነቱ] ተመልሶ፣ ህልውናው፡ ለአንዴ እና ለዘለዓለም፡ እንዲያበቃ ተደርጓል።

ይኸውም፡ በእውነተኛው ይኹን፣ ወይም፡ በሓሰተኛው ፍላጎታቸው እና ፈቃዳቸው፥ ምርጫቸው እና ውሳኔያቸው፡ "አርዑተ-ምንዥስናን [የምንዥስናን ቀንበር]፡ ከተቀበሉት መነኮሳት እና መነኮሳይያት በቀር"፡ ማለት ነው።

እነርሱ፡ የእኛ የእግዚአብሔር፡ የባሕርይ ሀብታችን የኾነውን፡ ሥርዓተ-ጋብቻንና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን፡ ሴትነትን እና ወንድነትን፥ ሩካቤ-ሥጋን እና ልደትን፤ ቅዱስ ቍርባንን እና ክህነትን፡ የመሳሰሉትንም ኹሉ፡ የሚፃረሩና የሚነቅፉ በመኾናቸው፡ ፈልገውና ወድደው፤ መርጠው እና ወስነው በተሸከሙት ቀንበራቸው ምክንያት፡ የማይቀርላቸውን እና የመረጡትን፡ እጅግ የተለያየ፤ የበዛም ፈተና እና ፍርኀት፡ እዚያው፡ ለእየራሳቸው እና በእየራሳቸው ላይ ብቻ ተከልሎ የሚቀር ይኾናል።

በአርዑተ-ምንኵስና ሥር የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችንን በሚመለከት፡ በእየራሳቸውም ላይ ኾነ፤ በሌሎች ላይ ስለሚደርሰው ፈተና እና መከራ፤ ችግር እና ሥቃይ፡ በእኛ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ሥር፡ ለመላው ፍጥረታችን ባለን፡ በእግዚአብሔር አባትነታችን እና እናትነታችን፥ ወንድምነታችንና እኅትነታችን፡ ሕይወታችን በኾነው መንፈስ-ቅዱስነታችን አማካይነት፤ ያለማቋረጥ የምናደርገውን፡ የቸርነት እና የምሕረት፤ የጥበቃና የምግብና ጸጋችንን እና ትሩፋታችንን እናጓድልባቸውም።

*፲. "__አዳም ሆይ! ሥራውን መጀመርን፡ አንተ፡ በሔዋን ላይ፡ እንዴት እንደምታደርግ እናሳይሃለን።' ብለው፡ አንዱም፤ ሌላውም፡ በአዳም ፊት፡ ክፉ ማድረግን /ሩካቤ-ሥጋ መፈጸምን/ ጀመረ።__ __ከዚህ በኋላ፡ አዳምን፦ 'አንተም፡ በሔዋን ላይ፡ እንዲህ አድርግ!' አሉት። 'ልጅ ትወልዳለህ፤ ዘር ትተካለህ፤ ትባዛለህም።' አሉት።__ ሰይጣን ይሸንግለው ዘንድም፡ በአዳም ፊት፡ ይህን ያደርግ ነበር።"* ተብሎ ስለተጻፈው፦

"መርገም እና ርኵሰት"፤ "ነውር እና ጸያፍ" ሊባል የሚገባው፡ በቀጥታ፡ ይህን የመሰለው፡ ሓሳዊው የመነኮሳት አጻጻፍ ነው እንጂ፡ እኛ እግዚአብሔር የሠራነውና የሠራንበት፥ ሕያዋን ፍጡሮቻችንም፡ ለዘለዓለማዊው የሰንበት ዓለማቸው እና ለቅድስቲቱ የትንሣኤ ሕይወታቸው፡ በመልካም መቀጠል፡ አስፈላጊና ጠቃሚ የኾነው፡ ሥርዓተ-ጋብቻ እና ከእርሱ ጋር የተያያዘው፡ ቅዱሱ ሩካቤ-ሥጋ አይደለም።

እንዲያው ለመኾኑ፡ አዳም እና ሔዋን፡ በዚያ፡ እግዚአብሔራዊ በኾነው የልዕልና እና የብፅዕና ተፈጥሮአቸው፡ ቀደም ብዬ፡ በየአርእስቱ እንደጠቃቀስሁት፡ ይህን ዓይነቱን፡ እንስሳትና አራዊት፤ አዕዋፍና ዓሣት ኹሉ፤ ሰዎች ጭምር፡ እንኳንስ ዐድገውና ነፍስ-ዐውቀው፤ ጐልምሰውም ይቅርና፤ ገና ከእናቶቻቸው ማሕፀን ወጥተው እንደተወለዱ፡ በግልገልነታቸው፤ እንደነገሩም ኹኔታ፡ በሕፃንነታቸው፡ ማንም ሳያሳያቸውና ሳያስተምራቸው፡ የሴት ወላጆቻቸውን ጡት ፈልገው የሚጠቡት እንዴት ነው? ሌላውንም ተከታታዩን የተፈጥሮ ግዳጅ ኹሉ የሚፈጽሙት፡ ማን አሳይቷቸውና አስተምሯቸው ነው? የየራሳቸውን የተፈጥሮ- ጠባይዓቸውን አመራር ብቻ ተከትለው አይደለምን? አዎን! ነው።

ታዲያ! አዳም፡ በዚያ ዕድሜውና የህልውና ልምዱ፡ ከእንስሳዊው የተፈጥሮ-ጠባዩና ከሰብአዊው የሥጋ ፍትወቱ ጋር፡ በተጨማሪ እና በበላይነት፡ እግዚአብሔራዊው የዕውቀት ጸጋ ስለነበረው፡ ከአንዲት ብቸኛ ሚስቱ ጋር፡ የሩካቤ-ሥጋ ግዳጁን ለመፈጸም የማያውቅና ዐቅሙ የሌለው ኾኖ፡ "እንዴት የሰይጣናት አስተማሪነትና አሳዩነት አስፈለገው!" ብሎ ለማሰብ፡ ለማንም አስተዋይ ሰብአዊ ተመልካች ይከብዳል።

ደግሞስ፡ ይህ ኹሉ ውርደትና ጥቃት፡ በአዳም እና በሔዋን ላይ፡ ከተወዳጁቸው ሰይጣናትም ቢኾን፡ እየደረሰባቸው ባለበት፡ በዚያን ጊዜ፡ እኛ እግዚአብሔር፣ እልፍ-አእላፋት ከኾኑት መላእክቶቻችን ጋር፡ ወዴት ነበርን? እንደዛሬው ኹሉ እኮ! ይልቁንም፡ በዚያን ጊዜም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነታችን፡ በዚያው እና በመላው፡ ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ፡ በምልዓት ኾነን እንገኝ፣ በነፍስ፣ በሥጋና በመንፈስ ህልው ኾኖ የሚኖረውን ፍጥረታችንንም፡ እንጠብቅና እንመራ፣ እንመግብና እናስተዳድርም እኮ ነበርን።

ከእኛ ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዝእተብሔር እም፡ "እንደአንዳችን ኹኑ!" ብለን፡ በወንድነት እና በሴትነት፣ በመልካችንና በአምሳያችን የፈጠርናቸው፡ እኒሁ አዳም እና ሔዋን፡ በገዛ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው በተከተሉት፡ የጥፋትና የክፋት ህልውናቸው ምክንያት፡ ከገነት ሕይወታቸው ወጥተው ቢሰደዱም፡ በዚያን ጊዜ፡ በምድር ላይ የነበሩት፡ ሥጋ-ለባሽ የሰው ፍጡሮች፡ እነርሱ ኹለቱ ብቻ በመኾናቸው፡ በእውነተኛ ንስሓቸው ከመመለሳቸው በፊትም ኾነ፣ እስኪመለሱም ድረስ ቢኾን፡ እየራሳቸው የሚያደርጉትን፣ በእየራሳቸው ላይና በአካባቢያቸው ጭምር፡ ይኾንና ይደርስ የነበረውን ኹሉ፥ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነታችን ሥር፡ በቅርብ እየተመለከትናቸው፡ እንደማንኛውም ፍጡራችን፡ እነርሱንም፡ በይበልጥ፡ እንጠብቃቸውና እንመግባቸው፣ እንመራቸውና እናስተዳድራቸው እንደነበረ ሊዘነጋ አይገባም።

## ለ"ገድለ-አዳም" ድርሳናቸው፡ ሓሳዊ ጥቅስ፡ አጠቃላይ መልስ።

አዎን! እኛ እግዚአብሔር፡ አስቀድመን፡ በሰማያት፡ በመለኮትነታችን፡ በሠራነውና በመሠረትነው፣ በእግዚአብሔር አብ እና በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ቅዱስ ከብካብ፡ አጽንተን በፈጸምነው፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓታችን ሩካቤም፡ እግዚአብሔር ቃልን እንደወለድነውና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንዳሠረፅነው፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ታምኖበት የተኖረ፡ ሃይማኖታዊ እውነት ነው።

እንደዚሁ ኹሉ፣ ኋላ፡ በመልካችንና በአርአያችን በአምሳላችንም፡ አዳምንና ሔዋንን፡ በወንድነትና በሴትነት ፈጥረን፥ "ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ! እነሆ! አዳም፡ ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!" የምታሰኘውንም፡ የመንፈስ-ቅዱስን ዕውቀት ሰጥተን፣ ቀደም ብለን፡ በሰማያት በመሠረትነው፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓታችን፣ አኹን ደግሞ፡ እነርሱን፡ በምድር ላይ፡ በትስብእታዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ በባልና ሚስትነት አንድ አድርገናቸው፡ እንግዴህ፡ "ብዝኍ! ወተባዝኍ! ብዙበት! ተባዙበትም!" ብለን፡ ባርከንና ቀድሰን በሰጠናቸው፡ በዚሁ ኹኔታ እየኖሩ የመቀጠላቸውንም ቊምነገር፣ ያው ሃይማኖታዊ እውነት እያረጋገጠ ያመለክታችኋል።

አኹን ምንባቡ በተሰማው ድርሳን ውስጥ የተነገረው ቃል ግን፡ ይህ፡ የፍጥረተ-ዓለም ውጥናችንና ግባችን፡ ለፍሬያማው ውጤት እንዲበቃ የኾነበትን፡ የጋብቻን ሥርዓት፣ ከእርሱ ጋር የተያያዘውንም የሩካቤ-ሥጋ ምግባሩን [የግብረ-ሥጋ ግንኙነቱን] እንዲህ፡ እንደኃጢኣት አድርጎ የማሳየቱ ሰይጣናዊ ሙከራ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሥርዓት የኾነውን ጋብቻን በማዋረድና በማርከስ፡ ሰይጣናዊ የኾነውን ምንኵስናን ግን፡ በማላቅና በመቀደስ፡ ይኸው አኹን፡ መነኮሳት፡ ለጵጵስና ሹመት የሚያበቃውን ክብር አጽንተው ለመቀጠል እንዲችሉ ለማድረግ፡ ኾን ተብሎ የተዘረጋ መሠሪ ዕቅድ መኾኑን አረጋግጦ ያሳያችኋል።

ይህ መሠሪ ዕቅድ፡ በተግባር ላይ እንዲውል፡ ለመነኮሳቱ፡ በብርቱ፣ በግድም አስፈላጊያቸው የሚኾነው ያለ ምክንያት አይምሰላችሁ! ምክንያቱን ላሳውቃችሁ፡-

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አቋም፣ አመራር እና አሠራር፡-

፩. እነርሱን፡ መነኮሳቱን፣ ለቤተ-ክህነቱ መንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ፡ ለካህንነትም ኾነ፥ ለሊቀ-ካህናትነት [ለጵጵስና] መርጦ በሚሾመው፣ የአጠቃላዩ አገልግሎት፡ ግንዱ ባለሥልጣን አካል በኾነው፡ በቤተ-ሕዝባችን ውስጥ፡ ሙሉ አባሎች የኾናችሁትን፡ እናንተን፡ ምእመናንና ምእመናት ልጆቻችንን፡ በነፍስም፣ በሥጋም፣ በመንፈስም፡ አስፈርተውና አሸቈጥቊጠው ለመግዛት እንዲመቻቸው ለማድረግ ነው፤

፪. የመንፈሳዊው አገልግሎት ዘርፍ በኾነው፡ በቤተ-ክህነታችን ውስጥ፡ ለሊቀ-ካህናቱ [ጵጵስናው] መንበር፡ ተመርጠው መሾም የሚገባቸው፡ በዚሁ፡ በእኛው፡ በእግዚአብሔራዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ ጸንተው የሚገኙት፡ ቀሳውስት ካህናቶቻችን [አገልጋዮቻችንን] ብቻ ሲኾኑ፣ ነገር ግን፡ በኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅ መነኮሳትና ጳጳሳት የበላይ ገዢነት ምክንያት፡ ይህ፡ መለኮታዊው እና ጥንታዊው የኢትዮጵያ ልጆቼ ሥርዓት ስለተወገደ፡ "ምናልባት ይኸው፡ ቅዱሱ፣ አገራዊው ሥርዓት፡ ሊመለስ ይችል ይኾናል!" ብለው በመሥጋት፡ እኒሁ፡ በእግዚአብሔራዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ ጸንተው የሚገኙት፡ ቀሳውስት ካህናቶቻችን፡ በጵጵስናው ሹመት በመሳተፍ፡ በምርጫው ሊወዳደሯቸው እንዳያስቡ፣ እንዳይቃጡም ለማድረግ ነው፤

፫. መነኮሳቱ፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ፡ የፈጸሙት ክህደት እና ዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነት እና ሌላውም ኹሉ ኃጢአት፡ በገሃድና በይፋ ስለኾነ፤ በእኛ በእግዚአብሔርም የሚተማመኑበት አንዳችም እምነት ስለሌላቸው፡ የሥጋዊው አገልግሎት ዘርፍ በኾነው፡ በቤተ-ምልክናችን ውስጥ ከተመደቡት የጊዜው መሰል-ገዢዎቻቸው ጋር በመመሳጠር፡ የየራሳቸውን፡ ሥጋዊ፥ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ሥልጣን ለማጠናከርና ለማስጠበቅ እንዲያመቻቸው ለማድረግ ነው።

መቼም፡ በምድር ላይና በሰዎች መካከል፡ ጥንትም፥ በአማካዩ ዘመንም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፥ ለዘለዓለምም፥ ምንጊዜም፡ የእግዚአብሔርን እውነት ገላልጣ የምታብራራና የዲያብሎስን ሓሰት አጋልጣ የምታወጣ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ብቻ ስለኾነች፡ አኹንም፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር የኾነው፡ ቅዱሱ የጋብቻ ሥርዓትና ከእርሱ ጋር የተያያዙት ቅዱሳት ምግባራት ምን እንደኾኑ፡ በመጠኑም ቢኾን፡ ያዘጋጀችላችሁ ሓተታ፡ እንደሚከተለው ቀርቦላችኋልና ስሙት!

ከኹሉ አስቀድሞ ልታውቁት የሚገባችሁ እውነታ፡ ጋብቻ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ ፆ፡ ጾታ ያልነበረው፡ አንድ ፈጣሪና አምላክ የኾነው እግዚአብሔርነታችን፡ መጀመሪያ፡ ራሱን፡ "እግዚአብሔር አብ" በሚል፡ በወንድነት [በባልነት] እና "እግዚአብሔር እም" በሚል፡ በሴትነት [በሚስትነት] ጾታ፡ ከኹለት ከከፈለ በኋላ፡ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን ለማስገኘት፡ የሠራውና ራሱ የፈጸመው፡ መለኮታዊ ሥርዓት መኾኑን ነው።

ይኸው፡ "ባልና ሚስት" የሚለው ስያሜና ግብር፡ ልክ፡ በዚያው በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት መልክና ይዘት፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያው፡ የፍጥረተ-ዓለም ጊዜ፡ ለፈጠራቸው አዳምና ሔዋን ከሰጣቸው፡ የአንድነት ህልውና ሥርዓት፡ የተገኘ ነው።

ታዲያ! እንዲህ ካልኾነ፡ ለምን፡ እንዲህ ተብሎ ተነገራችሁ፤ ተጻፈላችሁም? "ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ንግበር ሰብአ፡ <u>በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ!</u>

"ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው፡ <u>በአምሳለ-እግዚአብሔር። ተባዕተ፥ ወአንስተ፡ ገብሮሙ።</u> ወባረኮሙ እግዚአብሔር፤ ወይቤሎሙ፡- '<u>ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር!</u> ወቅንይዋ!

"ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ናሁ አዳም ኮነ፡ <u>ከመ አሐዱ እምኔነ፤</u> ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ።"

"ወበዕለት፡ አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም፡ በአምሳለ-እግዚአብሔር፡ ገብሮሙ፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ፤ ወባረኮሙ። ወሰመየ ስሞ፡ 'አዳም' በዕለት፡ እንተ ባቲ ፈጠሮሙ።"

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'ሰውን፡ በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር!' ይህንም ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የሕያዋን-እናት-ልጅን [ሰውን]፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረ። ወንድ እና ሴትም አደረጋቸው። 'ብዙ! ተባዙም! ምድርንም፡ ሙሏት! አቅኗትም!'

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'እነሆ፡ አዳም፡ መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ፡ ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!"

"እግዚአብሔር አዳምን፡ በእግዚአብሔር አምሳል በፈጠረው ቀን፡ ወንድ እና ሴት አደረጋቸው። ባረካቸውም። በፈጠራቸው ቀን፡ 'አዳም' ብሎ ጠራው።" (ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] ፩፥ ፳፮-፳፰፤ ፫፥ ፳፪። ፭፥ ፩-፪።)

አዎን! እውነታው፡ ይኸው፡ "ባልና ሚስት" የሚለው ስያሜና ግብር፡ ልክ፡ በዚያው በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት መልክና ይዘት፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያው፡ የፍጥረተ-ዓለም ጊዜ፡ ለፈጠራቸው አዳምና ሔዋን ከሰጣቸው፡ የአንድነት ህልውና ሥርዓት የተገኘ ስለኾነ ነው።

እውነታው ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ይኸው፡ "ባልና ሚስት" የሚለው ስያሜና ግብር፡ ለምን፡ እንደነውር፥ እንደጸያፍና እንደዓለማዊ ተቆጠረ? ተቆጥሮም፡ አንድ ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድን ላስገኘውና እግዝእተብሔር እም፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ላላት የአንድነት ግንኙነት፡ "ሚስት" የሚለው፡ የተቀደሰና ንጹሑ መለኮታዊ ቃል፡ ለምን፡ለእርሷ ብቻ እንዳይውል ተፈለገ?

ለምን፡ እንዲህ፡ ለእርሷ ብቻ እንዳይውል የተፈለገው፡ እግዚአብሔር ፈጥሮ የሠራውን፡ ራሱን፡ ቅዱሱንና ንጹሑን ጋብቻ፥ በእርሱም አማካይነት፡ የሚፈጸሙትንና እውን የሚኾኑትን፡ የቅድስናውንና የንጽሕናውን ምግባራት፡ ሰይጣንና ክፉ ሰዎች፤ በተለይም፡ መነኮሳት፡ በክፉው አስተሳሰባቸው፡ ወደሰይጣናዊነት እንዲለወጡና እንዲማስኑ በማድረጋቸው፥ ለዝንተ-ዓለም ሲያካኼዱ የኖሩትን፡ ይህንኑ የጥፋት ዘመቻቸውንም፡ ከግብ ለማድረስ በመፈለጋቸው መኾኑን፡ አጋልጦ ማሳወቅ ይገባል።

ይህን እውነታ ለማረጋገጥ፡ ከዚህ የሚከተሉትን የሓሰትና የክፋት ስያሜዎችና ግብሮች፡ በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡-

-በወንዱ አካለ ሥጋ ውስጥ፡ በእግዚአብሔር መልክና "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!" የተባለለትን፡ ሰውን የሚያህል ፍጡር የሚያስገኘውን፥ደግሞም፡ ፈጣሪ፡ በልዩ ጥበቡ የሠራውን፡ ቅዱሱንና ንጹሑን ዘር፡ "ኃጢአት" ብሎ፥

-በሴቷም አካለ ሥጋ ውስጥ፡ በማሕፀኗ ሽል ኾኖ፡ በእግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅ ሥራ የሚፈጠረውን፡ ያን፡ ቅዱስና ንጹሕ ዘር ተቀብላ፡ በፍጹም ሰውነት ለመፅነስ፡ የተዘጋጀች መኾኗን የምታበሥርበትን፡ ያን፡ ቅዱሱንና ንጹሑን የወር አበባ፡ "አደፍ፥ ጉድፍ፥ መርገምና ርኵሰት" ብሎ፥

-በቅድስናና በንጽሕና የተሸለሙትን፡ እነዚህኑ የፅንስ አካላትና ባሕርያት የሚያስገኙትን፡ የወንዱንም፥ የሴቲቱንም፡ የሰውነት አባላት፡ "አባለ-ዘር" እና "አፈ-ማሕፀን" ማለት ሲገባ፡ "ኀፍረተ-ሥጋ" ብሎ፤

-"ባል" የተባለው ወንዱ እና "ሚስት" የተባለችው ሴቷ፡ እግዚአብሔር፡ የተቀደሱና የተከበሩ፥ የነጹና ያማሩ አድርጎ በሠራቸው በእየብልቶቻቸው አማካይነት የሚያደርጉትን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ "ኃጢአት" ብሎ፡ በመፈረጅ፡ በዚያው፡ በክፉ ሰዎች ሰይጣናዊ አስተሳሰብ፡ በጋብቻና የእርሱ በኾኑት የባሕርይ ምግባራት ላይ፡ ለተካኼደውና እየተካኼደ ላለው ዘመቻ፤ ከተፈጸመውና እየተፈጸመም ላለው ጥቃት፡ እነዚህ የተጠቀሱት፡ ጥቂቶቹ ስሞችና ግብሮች፡ በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

ስለዚህ፡ እነዚሁ፡ "ባል"፤ የሚለው ቅዱሱና ንጹሑ መለኮታዊ ቃል፤ "ሚስት" የምትባለውም ቅድስትና ንጽሕት መለኮታዊት ቃል፡-

በአንድ ወገን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፥ የባልና ሚስት ነገርን የያዘውን፡ ሥርዓተ-ጋብቻንና ያገባ ወንድን፤ ያገባች ሴትንም ክብር፡ እያንኳሰሰና እያንቋሸሸ፥ እያረካከሰና እየረገመ ከሚያቃልለውና ከሚንቀው፥ ከሚያዋርደውና ከሚያወግዘው፤

በሌላው ወገን ግን፡ ኢእግዚአብሔራዊ የኾነውን አርዑተ-ምንኵስናን እያሞጋገሰና እያከባበረ፥ እያላቀና እያሞካሸ ካገነነውና ካነገሠው፥ ከቀደሰውና ካመለከው ሰይጣናዊ አስተሳሰብ የመነጨው ይትበሃል መኾኑን፡ የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ መለኮታዊ ሥርዓት የኾነው፡ ራሱ ቅዱሱ ጋብቻ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድና በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች ዘንድ ቀርቶ፡ "ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው፡ በግብዙ ኅብረተሰብም ዘንድ፡ እንኳንስ፡ ከሠሪው፥ ከፈጣሪው የተቀዳጀውን የቅድስናና የንጽሕና ክብርና ማዕርግ ሊያገኝ፥ የጋብቻው ፈጻሚዎችና ባለቤቶች የኾኑት፡ አዳማዊው ወንዱና ሔዋናዊቷ ሴቷ ጭምር፥ "ባልና ሚስት" ከሚለው መታወቂያ ስያሜያቸው ጋር፡ ይኸው እንዲህ፡ "የህልውና ማፈሪያዎችና የኃጢአት መገለጫዎች" እስከመባል ደርሰው፡ ኑሮአቸውን፡ በመሸማቀቅ ሲገፉ ይታያሉ።

ይኽ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ የተነሣ፡ በክፉው የዓለም ኅብረተሰብ መካከል፡ ከእግዚአብሔርዋ ደግነት ይልቅ፡ ሰይጣናዊው ክፋት፥ ከእግዚአብሔርዋ እውነት ይልቅ፡ ሰይጣናዊው ሓሰት [ኃጢአት]፥ ከእግዚአብሔርዋ ሕይወት ይልቅ፡ ሰይጣናዊው ሞት፡ በሰዎች ላይ፡ ዐይለውና ሠልጥነው ሲሠሩ እንደሚታዩ ኹሉ፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ያልሠራው አርዑተ-ምንኵስናም፡ እንዲህ፡ በክፉ ሰዎች ዘንድ፡ እግዚአብሔር ከሠራውና አክብሮ ከፈጸመው፡ ከሥርዓተ-ጋብቻ በላይ ተከብሮና ተፈላጊ ኾኖ፡ የአእምሮ ደካሞችንና ግብዞችን እንደልቡ ሲገዛና ሲያሰግድ ይታያል።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ ግን፡ የጋብቻ፥ የባልና ሚስትም ነገር፡ እንዲህ አይደለም።

ሥርዓተ-ጋብቻ፥ እንዲሁም፡ "ሚስት" እና "ባል" የሚሉት፡ ከእርሱ ጋር የተያያዙት ቃላት፡-

-ቅዱሱን ጋብቻ እንደሠሩትና እንደፈጸሙት፥ ደግሞም፡ የዚሁ የጋብቻ መገለጫዎች የኾኑትን፡ ቅዱሱን አዳምና ቅድስቲቱን ሔዋን፡ "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾኑ!" ብለው እንደፈጠሩት፡ እንደእግዚአብሔር አብ እና እንደእግዝእተብሔር እም፤

-እንዲሁም፡ የሕይወት አቋማቸውን እና የህልውና አካኼዳቸውን፡ እንደእግዚአብሔር አብ እና እንደእግዝእተብሔር እም በማድረጋቸው፤ አስቀድሞ፡ ሞትን ሳያይ እንደተሠወረው፡ እንደሄኖክ እና እንደሚስቱ፤ ከጥፋት ውኃ እንደዳነውም፡ እንደኖኅ እና እንደሚስቱ ሓይከል፤ እንደነዚህ ኹለት ባለትዳሮች፡ የተቀደሱና የተከበሩ፥ የተወደዱና የተመረጡ ኾነው፡ ለዘለዓለም የሚኖሩ ናቸው።

## ክፍል ሦስት።

## "ሕፃናተ-ገምኑዲን ፍጁ!" ተብለው የተላኩትን መላእክት በሚመለከት።

እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ በስሜ፡ "ኢትዮጵያውያን" እና "ኢትዮጵያውያት" ብላችሁ የምትጠሩ ወገኖች! ከቶ ምን ነካችሁ? "ዓዚም" የሚባለው የአፍዝ-አደንግዝ ሥራይ እንደተደረገባቸው እምነተ-ቢሶችና ደካሞች ሰዎች ኾናችሁ ለመገኘት፡ እንዴት ቻላችሁ? ከአዳም እና ሔዋን ፍጥረት ጀምሮ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!" ከዚያም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" በሚለው የስም-አጠራር የሚታወቁት ታማኞቹና ጽኑዎቹ ምዝላቶቻችሁማ፡ ይህን በመሰለው ምግባረ-ጥፉ ሥራ፡ እንኳንስ፡ እንዲህ፡ እንደእናንተ አድርገውት፡ እጅ ከፍንጅ ሊያዙበት ይቅርና፤ በወደረኞቻቸው ሰይጣናት ዘንድም እንኳ ቢኾን፡ አይጠረጠሩበትም፤ አይታሙበትም፤ በእኛም ዘንድ አይከሰሱበትም ነበር።

እናንተ ግን፡ ይኼን፡ በእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ የተቀዳጃችሁትን አምላካዊ ባሕርይ አሽቀንጥራችሁ በመጣል፡ እየራሳቸውን፡ በሓሰት፡-

፩. "የእስራኤል ልጆች ነን!" እያሉ በመመጻደቅ፡ ይፋ በኾነው የሃይማኖት ዘመቻቸው፡ ቀደም ብለው፡ ከዛሬ ሦስት ሽህ ዘጠኝ ዓመታት ጀምረው፡ በቅኝ አገዛዝ የያዟችሁ፡ ባዕዳኑና አሪታውያኑ አይሁድ፤

፪. ኋላም፡ እነርሱን ተከትለው፡ የዛሬ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠኝ ዓመታት አንሥተው፡ እንደነርሱ ኹሉ፡ በረቂቁ የሃይማኖት ወረራቸው፡ ሠርገው ገብተው፤ በዚያው፡ የቅኝ አገዛዝ ቀንበራቸው፡ ጠምደው የያዟችሁ፡ ባዕዳኑና ኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅ መነኮሳት፤ "ጳጳሳት" የሚነግሯችሁን ሓሰት ኹሉ፡ በድንቁርና ሞኝነትና በጭፍን ዕውርነት፡ ይኸው፡ ዝም ብላችሁ ተቀበላችሁት እኮ!

ይኹን እንጂ፡ ይህ ድርጊት፡ እንዴት፡ በቀላሉ፡ በእናንተ ዘንድ ታሳቢነትንና ተቀባይነትን አግኝቶ ሊኾንና ሊፈጸም እንደቻለ ለመረዳት፡ ለአስተዋዮች የሰው ልጆችም እንኳ ቢኾን ከብዶባቸውና አስገርሟቸው፤ እናንተኑ፡ ለከፍተኛ ትዝብት ዳርጓችሁ እንደኖረ፡ ልትገነዘቡት ይገባችኋል። ይህን እውነታ፡ እንዲህ በሚለው የእኔ ቃል የተከሠተው፡ የራሳችሁ አመለካከትና ድርጊት፡ እያረጋገጠ ይመሰክርባችኋል፦

ለመኾኑ፡ *"በቅዳሴ ጊዜ፡ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ ያወኩትን፡ ሕፃናተ-ገምኑዲን እንዲያጠፉ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ መላእክቶቻቸውን ሰደዱ!"* ብላችሁ፡ እንዴት ልታምኑና ይትበሃሉን ልትቀበሉት፥ ልታስተጋቡትም በቃችሁ? ነፍስንና ሥጋን፤ መንፈስንም፡ ሕያዋን አድርገን የፈጠርን፥ በሕይወትም የምናኖር፥ ራሱንም፡ በራሱ ፈቃድ ለሞት አሳልፎ የሰጠውን ምውቱን ሰው ሳይቀር፤ በአጠቃላይ፡ ሙታንን ኹሉ፡ በትንሣኤ እያስነሣን፡ ሕያው የምናደርገውን፡ <u>እኛን እግዚአብሔርን፡</u> የሞት አበጋዝ እንደኾንን ቆጥራችሁ፡ ቅዱሳን መላእክቶቻችንንም፡ ፍጡርን፡ ከሞት ለማዳን ፈጥነው-ደራሾች መልእክተኞች መኾናቸው ቀርቶ፡ ነፍስ-ገዳዮች፤ <u>ያውም፡ ምንም ያልበደሉ፤ ገና በንጽሓ-ባሕርይ ያሉ ሕፃናትን እንዲገድሉ፡</u> ከእኛ የተላኩ ጨካኞች ደም-አፍሳሾች እንደኾኑ ቆጥራችሁ፡ ይህን የመሰለውን፡ ሓሳዊ ብቻ ሳይኾን፡ ከሳሽና ኩናኝ የኾነ፡ የውንጀላ ዘለፋን፡ እንዴት ልትሠነዝሩብን ደፈራችሁ?

እንዲያው ለመኾኑ፡ ይህን የመሰለው ግብር፡ የማነው? እንኳንስ፡ "እኛን እግዚአብሔርን እናውቃለን፤ እናምናለን፤ እናገለግላለንም!" በምትሉት፡ በእናንተ ዘንድ ቀርቶ፡ እኛን እግዚአብሔርን በማያውቁን አረማውያንና "ጠቢባን ነን!" በሚሉ ወገኖች ዘንድ ኹሉ እንኳ፡ ይህን የመሰለው ግብር፡ የማን እንደኾነ፡ በግልጽ የሚታወቅ አይደለምን? አዎን! ይታወቃል። እርሱም፡ <u>*የዲያብሎስና የሠራዊቱ ብቻኛ ግብር መኾኑ ነው።*</u>

እየራሳችሁን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" ብላችሁ የምትጠሩት፡ እናንተ ሳትቀሩ፡ በዚህ፡ ገሃድ ኃጢአት፡ ዐባሪ-ተሳታፊ ኾናችሁ ከተገኛችሁማ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እንዴት አድርጌ፡ እናንተንስ፡ "ልጆቼ!" ብዬ ልጠራችሁ የሚቻለኝ ይመስላችኋል? እያንዳንዳችሁ፡ በነፍስ ወከፍ፡ በምርና በጥብቅ፡ ልታስቡበት፤ ንስሓም ገብታችሁ፤ ምግባራችሁን ልታቃኑ የሚገባችሁ፡ ዓቢይ ቍም-ነገር ነው።

## ሕፃናት፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸው ቅርበት፣
## ስለእነርሱም የተናገረላቸው ቃላት።

አኹን፡ በዚሁ የሕፃንነት ዕድሜ ያሉት እና ወደፊትም፡ የሚገኙት ብቻ ሳይኾኑ፡ እናንተ፡ ዛሬ፡ በትልቅ ሰውነት የምትገኙ፡ ወንዶችም፣ ሴቶችም ጭምር፣ ኹላችሁም፡ ሕፃንነትን ያለፋችሁበት ስለኾነ፡ ስለሕፃንነት፡ ምንም ልነግራችሁ የሚያስፈልግ አይደለም። ከልደት አንሥቶ፡ "ነፍስ-ማወቅ" እስከሚባለው የዕድገት ደረጃ ድረስ ያለው የዕድሜ ክልል፡ **ሕፃንነት** ነው።

አዎን! በዚህ የሕፃንነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሕፃናት፡ ደጉንና ክፉውን፥ እውነቱንና ሓሰቱን፣ "ሕይወት"ን የሚያስገኘውን ጠቃሚውንና "ሞት"ን የሚያስከትለውን፡ ጎጂውንም፡ ፈጽመው ለይተው አያውቁም። የሚያውቁት ነገር ቢኖር፡ ደጉንና እውነት የኾነውን፣ እንዲሁም፡ ሕይወትን የሚያስገኘውን ጠቃሚውን ብቻ እንጂ፡ ክፉውንና ሓሰት የኾነውን፣ እንዲሁም፡ ሞትን የሚያስከትለውን ጎጂውን አይደለም። አዳምና ሔዋን፡ የኋላ ኋላ፡ እኒህን ኹሉ ያሳወቀቻቸውን፡ እናንተ፡ "ዕፀ-በለስ" የምትሏትን፡ የዕውቀት ዛፍ ከመብላታቸው በፊት፣ ያውቋቸው የነበሩትን፡ ደጉንና እውነት የኾነውን፣ እንዲሁም፡ ሕይወትን የሚያስገኘውን ጠቃሚውን ብቻ ማለት ነው። ስለዚህ፡ በእነርሱ ዘንድ፡ ምንም ዓይነት ክፋትና ሓሰት፣ ጥፋትና ጉዳት ሳይኖሩ፡ ኹሉን የሚያደርጉት በመልካምና ለመልካም ብቻ ነው። ይህን እውነታ፡ ኹላችሁም ዐውቃችሁት፡ በተፈጥሮአዊውና በሃይማኖታዊው እውነተኛነቱ ተቀብላችሁ የምታምኑበት ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ሕፃናት፡ በሕፃንነት ዕድሜያቸው በሚያደርጉት ኹሉ፡ እንኳንስ፡ በእኛ በእግዚአብሔር እና በመላእክቶቻችን ዘንድ፡ በሰይፍ ስለት ተቀሥፈውና ታርደው እንዲገደሉ የይሙት-በቃ አምላካዊ ፍርድን የሚያሰጥባቸው ኃጢአት ኾኖ ሊቆጠር ቀርቶ፣ የእናንተን የቍንጥጫን ቅጣት እንኳ ሊያመጣባቸው የሚገባ እንዳልኾነ፡ ጤናማ በኾነ፡ በማንኛውም ሰብአዊ ፍጡራችን ዘንድ ይታመናል።

እኛም እግዚአብሔር እኮ፡ በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም እና በልጇ-በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት፡ በዚህ ፍጥረተ-ዓለማችን ምድር ላይ፡ በሰዎች ፍጡሮቻችን ዘንድ ተገልጠን፡ በመካከላችሁ በተመላለስን ጊዜ፡ ስለሕፃናት የተናገርናቸውን ቃሎቻችንን ታስታውሷቸው የለምን? በልጇ-በወዳጇ ከተነገሩት ከእነዚያኑ ቃላት መካከል፡ እስኪ ዛሬ ደግሞ፡ በእኔ አንደበት፡ ጥቂቶቹን ላሰማችሁ!

*፩. "ወበይእቲ ሰዓት፡ ቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ፡ ለእግዚእ ኢየሱስ፡ እንዘ ይብሉ፡- 'መኑ እንጋ፡ የዐቢ፡ በመንግሥተ-ሰማያት?' ወጸውዐ ሕፃነ፣ ወአቀሞ ማእከሎሙ።*

"ወይቤ፦ 'አማን እብለክሙ! እመ ኢተመየጥክሙ፣ ወኢኮንክሙ፡ ከመ ዝንቱ ሕፃን፡ ኢትበውኡ ውስተ መንግሥተ-ሰማያት። ወዘአትሐተ ርእሶ፡ ከመ ዝንቱ ሕፃን፡ ዝ ውእቱ ዘየዐቢ፡ በመንግሥት-ሰማያት። ወዘሂ ተወክፈ አሐደ፡ ዘመጠነዝ ሕፃን በስምየ፣ኪያየ ተወክፈ። ወለዘሂ አስሐቶ ለአሐዱ፡ እምእሉ ንኡሳን፡ እለ የአምኑ ብየ፡ ይኄይሶ፡ ከመ ይእስሩ በክሳዱ፡ ማሕረጸ-አድግ፤ ወያስጥምዎ፡ ውስተ ልጐተ-ባሕር። ...ዑቁ! ኢታስተሐቅርዎ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን! እብለክሙ፣ ከመ መላእክቲሆሙ በሰማያት፡ ወትረ ይሬእዩ ገጾ ለአቡየ ዘበሰማያት።

"በዚያች ሰዓት፡ ደቀ-መዛሙርቱ፡ ወደእርሱ፡ ወደእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ቀርበው፡ 'በእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ከኹሉ የሚበልጥ፡ እንጃ! ማን ይኾን?' ሲሉ ጠየቁት። እርሱም ሕፃን ጠርቶ፡ በመካከላቸው አቆመና፣ 'እውነት እላችኋለሁ፤ ካልተመለሳችሁ፤ እንደዚህ ሕፃን ካልኾናችሁም፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም። ራሱን፡ እንደዚህ ሕፃን፡ ትሑት የሚያደርግ፡ ይህ ነው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ከኹሉ የሚበልጥ። ማንኛውንም ሰው፡ እንደዚህ ሕፃን አድርጎ፡ በስሜ የሚቀበል ኹሉ፡ እኔን እንደተቀበለኝ እቆጥርለታለሁ። በእኔ ከሚያምኑት፡ከእነዚህ፡ ከታናናሾቼ መካከል፡ አንዱን ያሳተ ሰው ቢኖር፡ ያ አሳች፡ የወፍጮ ድንጋይ፡ በአንገቱ ታስሮ፡ ወደጥልቅ ባሕር ቢሰጥም በተሻለው ነበር። ...ዕወቁ! ከእነዚህ፡ ከታናናሾቹ መካከል፡ አንዳቸውንም ቢኾን፡ [መምታት፥ ወይም፡ መግደል ቀርቶ] እንዳታቃልሉና እንዳትንቁ፣ እንዳትነቅፉና እንዳትጸየፉም ተጠንቀቁ! ሰማያውያን የኾኑት መላእክቶቻቸው፡ በሰማያት ባለው፡ በአባቴ ፊት፡ በየጊዜያቸው እየቀረቡ፡ ስለእነሱ ያስታውቃሉና፤ ያመለክቱማል፣ ይማልዱማል።' አላቸው።" (ማቴ. ፲፰፥ ፩-፯።)

፪. "ወአምጽኡ ኀቤሁ ሕፃናተ፡ ይግሥሦሙ፤ ወያንብር እዴሁ ላዕሌሆሙ። ወርእዮሙ አርዳኢሁ፤ ገሥጽዎሙ፡ ለእለ አቅረብዎሙ። ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ፤ ተምዐ፤ ወጸውዖሙ፤ ወይቤሎሙ፦ 'ኅድጉ ሕፃናተ፣ ይምጽኡ ኀቤየ! ወኢትክልእዎሙ! እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ-እግዚአብሔር። አማን እብለክሙ! ዘኢተቀበላ ለመንግሥተ-እግዚአብሔር፡ ከመ ዘሕፃናት፡ ኢይበውኣ። ወአንበሮሙ ውስተ ሕፅኑ፤ ወባረኮሙ፤ ወወደየ እዴሁ ዲቤሆሙ።

"ይዳስሳቸው፣ እጁንም፡ በላያቸው ያኖር ዘንድ፡ ሕፃናትን፡ ወደ እርሱ አመጧቸው። ደቀ-መዛሙርቱም፡ ይህን ሲያዩ፡ ያቀረቧቸውን ወላጆቻቸውን፡ 'ለምን አመጣችኋቸው?' ብለው ገሠፁዋቸው። እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስም፡ ይህን ባየና በሰማ ጊዜ፡ ተቆጣ፤ ጠርቶም፡ እንዲህ አላቸው፦ 'ሕፃናቱ፡ ወደእኔ ይመጡ ዘንድ ተውዋቸው! አትከልክሏቸው! የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንደእነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ! የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ ራሱን፡ እንደሕፃናት አድርጎ የማይቀበላት፡ አይገባባትም።' በጭኑም ላይ አስቀመጣቸው፤ እጁንም በላያቸው እያኖረ ባረካቸው።
(ማር. ፲፥ ፲፫-፲፮። ሉቃ. ፲፰፥ ፲፭-፲፯።)

፫. "ወሶበ ርእዩ ሊቃነ-ካህናት፥ ወጸሓፍት፡ መንክረ ዘገብረ፣ ወደቂቅኒ፡ እንዘ ይጸርሑ በቤተ መቅደስ፣ ወይብሉ፡- 'ሆሣዕና፡ ለወልደ-ዳዊት!' ኢሐወዞሙ፤ አላ አንጐርጐሩ። ወይቤልዎ፡- 'ኢትሰምዕኑ ዘይብሉ፡ እሉ ደቂቅ?' ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ፡- 'እወ! አልቦሁ፡አመ አንበብክሙ ዘይቤ፡- ‹እምአፈ-ደቂቅ፥ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሓተ።›'"

"የአይሁድ የካህናት አለቆችና ሊቆች፡ በሆሣዕና ሕዝባዊ የይባቤ ጉዞ ላይ የኾነውን ድንቅ ነገር ኹሉ ባዩ ጊዜ፣ ልጆችም፡ በቤተ-መቅደስ፡ 'ሆሣዕና፡ ለዳዊት ልጅ!' እያሉ በጩኸት ድምፅ የሚዘምሩትን የስባሔ ቃል በሰሙ ጊዜ፡ ባዩትና በሰሙት፡ ተቆጥተው፡ አንጐራጐሩ እንጂ፣ አልተደሰቱም። እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስንም፡- 'እኒህ ልጆች የሚሉትን አትሰማምን?' አሉት። እርሱም፡- 'አዎን! እየሰማሁ ነኝ። እናንተ ግን፡ «እናውቃለን! ‹ቅዱሳት› የምትሏቸውን መጻሕፍቶቻችሁንም እናነባለን!» ትላላችሁ እንጂ፡ ያወቃችሁና ያነበባችሁ ብትኾኑ ኖሮ፡ 'ምስጋናን፡ [ሊያቀርቡልኝ የሚገባቸው፡ ይህን ባያደርጉ]፡ ከልጆችና ከሕፃናት አንደበት፡ ለራሴ አዘጋጀሁ!' የሚለውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ ባወቃችሁ፣ ባነበባችሁም ነበር። ስለዚህ፡ ማስተዋሉ የላችሁም።" አላቸው። (ማቴ. ፳፩፥ ፲፭-፲፮።)

ያ፡ አሥቃቂ፡ የሓሰት ዝክረ-ነገር ተጽፎ ሲነበብና ሲነገር የተኖረው፡ እንዴት እንደኾነ፡ እናንተም ደግሞ እዩት! ተመልከቱትም! አዳምጡት! አስተውሉትም! እንግዴህ፡ እንዲህ ተብሎ፡ በእኛ በእግዚአብሔር መለኮታዊና ሕያው ቃል የተነገረላቸውን ፍጹማን ንጹሓን ሕፃናቶቻችንን ነው፣ እነሆ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በዲያብሎስ ተመስለን፣ በቅዱሳት መላእክቶቻችን ሰይፍ እየተመቱ እንዲገደሉ፣ እንዲያልቁም እንደወሰንን ተደርጎ የተጻፈው። እኒህ ፍጡሮቻችን፣ ፍጡሮቻችን ብቻ ሳይኾኑ፡ ልጆቻችንና ነጋሢዎቻችን፣ ካህናቶቻችንና ዜጎቻችን አድርገን፡ በመልካችንና "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኹናችሁ!" ብለን፡ በነፍስ፣ በሥጋና በመንፈስም የወለድናቸው ናቸው። መላእክቶቻችንም ይህን፡ የግድያ ግዳጅ እንዲፈጽሙ፡ በትእዛዝ እንደላክናቸው፣ እነዚሁ መላእክቶቻችንም፡ የእኛን ትእዛዝ ተከትለው፡ የርኵሳን መናፍስትን ግብር እንደፈጸሙ ተቆጥሮ፡ በአኹኑ ዘመንም እንኳ ሳይቀር፡ ይኸው፡ ዛሬም፡ በሰፊው እየተነገረና እየተተረጐመ፣ በብዛትም እየተጻፈና እየታተመ፣ እየተራባና እየተሠራጨ፥ እየተነበበና እየተሰማ ያለው።

ከዚሁ ዝክረ-ነገር ጋር የተያያዘ ቍርኝትና ጠንቅነት ካላቸው ጎጂ ልማዶች መካከል፡ እዚህ ላይ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ብዙዎች አሉ፤ ከእነዚህ አንዱን ብቻ ባወሳው፡ *"በቅዳሴ ጊዜ፡ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ አውከው ነበር እና ይቀሠፉ!* [በመላእክት ሰይፍ ይገደሉ!]" ከተባሉት ጋር፡ በዚህ ረገድ፡ ዕብረው እንዲፈጁ የተፈረደባቸው ሕፃናት የመኖራቸው ነገር ነው።

እነዚህም፡ ራሱን፡ ቅዱሱን ቍርባን፣ ይኸውም፡ ልጇ-ወዳጇ፡ ከእኔ የወረሰውን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፣ ሊቀበሉት የሚያስፈልጋቸውና የሚገባቸው፡ ብዙዎች ትልልቆች እያሉ፡ እነዚያ ተትተው፣ የማያስፈልጋቸው፣ ቢያስፈልጋቸውም እንኳ፡ ፍጹም የበቁት ሕፃናት፡ የቅዳሴው ሥርዓት ተጀምሮ እስከሚያበቃበት ድረስ፡ ባለው በረዥሙ የሰዓቶች ጊዜ፡ የእናቶቻቸውን ጡት እንኳ እንዳይጠቡ በመከልከላቸው፡ ከሚደርስባቸው መወራጨት ይልቅ፣ በይበልጥ፡ ከሚያሰሙት ከፍተኛና የማያቋርጥ የልቅሶ ጩኸት የተነሣ፡ የቅሥፈቱ [የግድያው] ሰለባዎች መኾናቸው ጭምር ተረጋግጦ የሚነገረው፡ አስፈሪው የፍርጃ ቃል ነው።

## ሓሳዊው እና ልበ-ወለዱ ይትበሃል፡ ምን እንደሚል።

እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ ያለውን፡ ትክክለኛውንና እውነተኛውን ዝክረ-ነገር፡ ለእናንተ ከመንገሬ በፊት፡ በእነዚሁ፡ ኦሪታውያን አይሁድና ኦርቶዶክሳውያን ግብፆች በኾኑት ጉዶች ዘንድ፡ ተጽፎ የሚነገረው፡ ይኸው፡ ሓሳዊና ልበ-ወለድ ይትበሃላቸው፡ ምን እንደሚል፡ እስኪ፡ አስቀድማችሁ ስሙት! አንብቡትም!

እርሱም፡ "**ቅዳሴ-ማርያም**" ብለው፡ በስሜ ሰይመው በሚጸልዩበት መጽሓፋቸው ውስጥ፡ "**ወብኪ ተሐደሰ፡ ቀዳሜ ኵሉ ፍጥረት።** የፍጡሮች ኹሉ መነሻ መደቦች የኾኑት፡ እሳት[ፀሓይ] እና ነፋስ፣ ውኃ እና መሬት የታደሱብሽ አንቺ ነሽ።" ለሚለው የሙገሳና የምስጋና ቃል፡ በአንድምታ ትርጓሜያቸው፡ እንዲህ ሲሉ፡ የሰጡት ሓተታቸው ነው፡-

"ግብር እምግብር ከተፈጠሩ ፍጥረታት አስቀድሞ፡ *ዐራቱ ባሕርያት የታደሱብሽ አንቺ ነሽ።"* ከሚለው፡ ነጠላ ትርጓሜያቸው በኋላ፡ የሓተታ ትርጓሜያቸውን እንዲህ በማለት ይቀጥላሉ፡- *"'ነፋስ፡ ኀዩል፤ እሳት፡ ኀዩል፤' ይላል፤ ኹሉንም፡ በያሉበት አምልከዋቸው ነበር፤ መመለካቸውን ብልየት [እርጅና]፣ አለመመላካቸውን፡ ተሓድሶ አድርጎ፣ እንዲህ አለ።"* ይሉና፡ ሌላውን ሓተታ ሲያቀርቡ፣ *"አንድም፡ ከልጆቹ አስቀድሞ የነበረ አዳም፡ የታደሰብሽ፡ አንቺ ነሽ።"* ያሉትን ደግሞ፡ *"አዳም፡ ዕፀ-በለስን በልቶ፡ ብልየት አግኝቶት ነበረ፤ በእመቤታችን* [በድንግል ማርያም] *ተሐድሶን ሰላገኘ፤"* ብለው የአንድምታ ትርጓሜያቸውን ያስፋፉታል።

በመጨረሻ፡ *"አንድም፡ ከፍጥረቱ ኹሉ አስቀድሞ የነበረ መልአኩ የታደሰብሽ አንቺ ነሽ።"* የሚለውን፣ ዋናውን፡ የአንድምታ ትርጓሜያቸውን ሓተታ፡ *"'ቀውስጦስ' የሚባል መልአክ አስታርቃለችና።"* በሚል መግቢያ፡ ትረካቸውን፡ እንዲህ ሲሉ በመቀጠል ያጠቃልሉታል፡-

*"ይህስ፡ እንደምን ነው? ቢሉ፣ ጌታ* [እግዚአብሔር] *'ሕፃናተ-ገምኑዲን አጥፉ!' ብሎ፡ መላእክትን ሰደደ። የኒህስ ሕፃናት፡ 'ዕዳቸው፡ እንደምን ነው?' ቢሉ፡ አልታወቀም። አንድም፡ ታውቋል፤ እሱም፡ "<u>በቅዳሴ ጊዜ፡ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ አውከው ነበር።</u>*

*"ቀውስጦስ፡ መልከ-መልካም ሕፃን፡ ከነማርዳው አገኘ። 'ለዝሰ፡ ዘፈጠሮ ይቅትሎ! ይህንስ፡ የፈጠረው ይግደለው!' ብሎ ትቶታል። የቀሩት መላእክት፡ የተላኩበትን ፈጽመው ሲያርጉ፤ እርሱ፡ኃይል ተነሥቶት ቀረ። አሻግሮ ቢያይ፡ በደብረ-ቀልሞን፡ ዐምደ-ብርሃን ተተክሎ አየ። 'ዛቲ መካን፡ ትከውነኒ አራቂተ፡ ምስለ እግዚእየ! ከፈጣሪዬ እግዚአብሔር ጋር የምታስታርቀኝ፡ ይህቺ ቦታ ናት!' ብሎ፡ ተጎትቶ ኼዶ፣ ከደጅ ብርሃን ወደቀ።*

*"ዲያቆን፡ ለተልእኮ ከፍቶ ቢገባ፣ ከዚያ ወድቆ አገኘው። 'አንተ፡ ምንድር ነህ? ምድራዊ ነህ? ወይስ፡ ሰማያዊ ነህ?' አለው። ግብሬ፡ ምድራዊ አድርጎኝ ነው እንጂ፡ ተፈጥሮዬስ፡ ሰማያዊ ነው!' አለው። 'እኹንም፡ ኼደህ፡ ለአባ ሳሙኤል ንገርልኝ!' አለው። ኼዶ ነገረው። እርሱም፡ መጥቅዕ [ደወል] መትቶ፣ ሕዝቡንም ሰብስቦ፣ 'ፃ፩ እግዚኦታ! ፃ፩ በእንተ-ማርያም!' አድርሶ፣ ኼዶ፡ ከሥዕለ-ማርያም ተማፀነ።*

*"[ሥዕሊቱም፡-] 'በቀኝ እጅህ፡ ቀኝ ክንፉን፣ በግራ እጅህ፤ ግራ ክንፉን ይዘህ፡ ‹ተንሥእ፣ በስመ-እግዚአብሔር አምላክከ! በፈጣሪህ፡ በእግዚአብሔር ስም ተነሥ!› በለው!' አለችው። ኼዶ፡ 'በቀኝ እጁ፡ ቀኝ ክንፉን፣ በግራ እጁ፤ ግራ ክንፉን ይዞ፡ ‹ተንሥእ፣ በስመ-እግዚአብሔር አምላክከ! በፈጣሪህ፡ በእግዚአብሔር ስም ተነሥ!› ቢለው፡ የቀደመ ኃይሉ ተመልሶለት፣ 'በረድኤት እንዳልለያችሁ፡ ስሜን፡ ከአባ ሳሙኤል አትለዩት!' ብሏቸው፡ ዐርጓል።"*

ታዲያ! እናንተ ግብዞችና ጉዶች፡ ይህን፡ የዲያብሎስንና የሥራዊቱን ጠንቀኛ ክፉ ግብር፣ እንዲህ፡ ለእኛ ለእግዚአብሔር እና ለመላእክቶቻችን አዛውራችሁ፡ የምታስቡትና የምትናገሩት፣ የምትቀበሉትና የምታምኑበት፣ የምታስቀምጡትና የምትጽፉት፣ ከዚህም ኹሉ አልፋችሁ የምታስተጋቡትና የምታስተምሩት እስከሚኾን፡ እንዴት ሊደርስ ቻለ!? ይህ ኹኔታችሁ፡ እንዴት ሊደርስና ሊኾን እንደቻለ የሚያስረዳው ዝክረ-ነገራችሁ፡ ለሰሚዎች የዓለሙ ሰዎች እንኳ ሳይቀር፡ እጅግ አስደንቋል፤ አሳዝኗልም።

በዚህ የሓሰት ልብ-ወለድ ታሪክ ውስጥ፡ ኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅ መነኮሳትና ጳጳሳት፡ የሥዕለ-ማርያም አምልኮን በሚመለከት፡ ቀውስጦስ፡ "*ለአባ ሳሙኤል ንገርልኝ!"* *ያለው ዲያቆን፣ "ኼዶ ነገረው።*

*"እርሱም* [አባ ሳሙኤል]፡ *መጥቅዕ [ደወል] መትቶ፣ ሕዝቡንም ሰብስቦ፣ 'ሣ፭ እግዚኦታ! ሣ፭ በእንተ-ማርያም!' አድርሶ፣ ኼዶ፡ ከሥዕለ-ማርያም ተማፅኖ።*

"[ሥዕሊቱም፡-] *'በቀኝ እጅህ፡ ቀኝ ክንፏን፤ በግራ እጅህ፤ ግራ ክንፏን ይዘህ፡ ‹ተንሥእ፣ በስመ-እግዚአብሔር አምላክከ! በፈጣሪህ፡ በእግዚአብሔር ስም ተነሥ!› በለው!' አለችው።"* ብለው የጻፉት ነገራቸው፡ ለራሳቸውና ለተከታዮቻቸው፡ በራሳቸው የፈጠሩት የአምልኮ ፈሊጥ እንጂ፡ እኔ የፈቀድሁት፣ የምቀበለውም አይደለም።

ይህን የመሰለው የሥዕል አምልኮ፣ "**እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።** እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነውና፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ይገባቸዋል።" ያለውን፡ በልጅ፣ በወዳጅ፣ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተነገረውን ቃል የሚፃረር ነውና። (ዮሓ. ፬፥ ፳-፳፬።)

በዚያ፡ የኢትዮጵያዊት ልጃችን የንግሥቲቱ ሕንደቄ ጃንደረባ በነበረው፡ እናንተ፡ "ባኮስ" በምትሉት፡ በታመነው ልኡካችን፡ በኢትዮጵያዊው የአዲስ ኪዳኑ "አቤሜሌክ" ሃይማኖታዊ ምግባር ተረጋግጦ እንደተመሰከረው፡ "**ብፁዓንሰ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ፡ የአምኑኒ!** ብፁዓንስ፡ ሳያዩ የሚያምኑብኝ ናቸው!" የተባለላቸውና በትክክለኛው እግዚአብሔራዊ አምልኳቸው የማይጠረጠሩት እውነተኞቹና ታማኞቹ የቃል ኪዳን ልጆቼ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ ከዚህ የተነሣ፡ ይህን የመሰለውን የሥዕል አምልኮ፣ ከጥንት ጀምሮ፡ እንደጣዖት አምልኮ ቆጥረውት የሚጸየፉት እንጂ፡ ፈጽመው፡ በሃይማኖት ተቀብለው፣ በምግባር የሚፈጽሙት አይደለም። የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳትና ጳጳሳት፡ የቅኝ ገዢነት ሥልጣን፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ላይ፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ሳይቀር፡ የቱን የሚያህል፡ ኃይለኛ ተፅዕኖን እንዳደረገባቸው፡ ራሱ ዛሬ ያለው ኹኔታ፡ በገሃድ እያረጋገጠ ያሳያችኋል። (ዮሓ. ፳፥ ፳፱።)

## "ሕፃናተ-ገምኑዲን ፍጁ!" ተብለው ከተላኩት መላእክት፣ አንዱ የኾነው፡ የቀውስጦስ፡ እውነተኛ ዝክረ-ነገር።

እንግዴህ፡ *"ሕፃናተ-ገምኑዲን ፍጁ!"* ተብለው የተላኩት መላእክት፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር እንደተላኩ ቅዱሳን ተደርጎ፡ ይኸው እንዲህ፡ በቃል ሲነገር፣ በብራናም ተጽፎ ሲነበብ የተኖረው ታሪክ፡ ሓሳዊና ሰይጣናዊ መኾኑ፡ እስካኹን በነገርኋችሁ ቃሌ ተረድታችሁታል። እንዲህ ከኾነ፡ እውነተኛውን ላሳውቃችሁ ያስፈልጋችኋል።

*መቸም፡* የሓሰት አባት የኾነው ዲያብሎስና ሠራዊቱ አጋንንት፥ እርሱን መስለው የተከተሉት፡ ሰይጣናት የኾኑ ሰዎችም፡ ብዙው ዓይነት የክፋት ግብራቸው ይታወቃል።

ከዚያ ውስጥ፡ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል፡ ጣፋጩን፡ ወደመራራ፣ ቀናውን፡ ወደጥመት፣ ፍቅሩን፡ ወደፀብ፣ ሰላሙን፡ ወደጦርነት፥ ብርሃኑን፡ ወደጨለማ፣ በረከቱን፡ ወደመርገም፣ በይበልጥና በተለይም፡ **እውነቱን፡ ወደሓሰት፥ ደጉን፡ ወደክፉ፣ ሕይወትን፡ ወደሞት፡** መለወጥና መቀየር፡ ቀዳሚ ተግባራቸውና ዋና ሙያቸው በመኾኑ እንጂ፡ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳትና ጳጳሳት ተነግሮ የሚሰማው፣ ተጽፎም የሚነበበው፡ የሕፃናተ-ገምኑዲ የዕልቂት ታሪክ፣ የደረሰና የተደረገ፡ ትክክለኛና እውነተኛ ዝክረ-ነገር ኾኖ አይደለም።

እስካኹን የሰማችሁት፡ ይህ ትረካ፡ የእነርሱው፡ የሓሳውያኑ ሲኾን፣ **እውነተኛውንና ትክክለኛውን ዝክረ-ነገር ደግሞ፡ እንግዴህ፡ ከእኔው አንደበት ስሙት!** እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው:-

እየታረዱ እንዲያልቁ የተፈረደባቸው፣ "ሕፃናተ-ገምኑዲ" የተባሉት ሰለባዎች፡ ለሕፃኑ ኢየሱስ መሲሕ ቤዛ ኾነው፡ በርኩሳኑ መናፍስት አለቃ፡ በዲያብሎስና በክፉዎቹ የአይሁድ ንጉሥ፡ በሄሮድስ ሰይፍ፡ እየታረዱ ያለቁት፡ "**ሕፃናተ-ቤተ-ልሔም፡ ዘይሁዳ**" ናቸው። በአንድ በኩል፡ ሄሮድስ፡ ኹለት ዓመትና ከዚያ በታች የኾኑ ሕፃናተ-ቤተ-ልሔምን እንዲፈጁ፡ ጨካኞች ወታደሮቹን እንደሰደደ ኹሉ፣ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በተለያየ ክለላ ምክንያት፡ ከዚያ፡ ከሄሮድስ ሰይፍ አምልጠው የተረፉ ሕፃናት ቢኖሩ እንኳ፡ አንዳቸውንም ሳያስቀሩ፡ ኹሉንም፡ ፈጽመው እንዲጨርሷቸው፡ በሓሳውያኑ ይትበሃል ውስጥ፡ "መላእክት" የተባሉትን፡ ርኩሳን መናፍስቱን የላከው ሄሮድስን፡ ለዚያ ግፍ ያነሣሣው፡ ያው ዲያብሎስ ነው። "ቀውስጦስ" የተባለው ርኩስ መንፈስ፡ ከእነዚያ የርኩሳን መናፍስት ሥራዊት፡ አንዱ ኾኖ የተገኘው ነው።

ቀውስጦስ፡ ራርቶ የተወው <u>ሕፃን</u>ስ፡ ማን መሰላችሁ? እኛ እግዚአብሔር በምንቀበለው፡ በእውነተኛው የመንፈስ-ቅዱስ አምልኳቸው፡ በንጽሕናና በቅድስና፡ እስከእርጅናቸው፡ በምክነት ኖረው፡ ከዚያ፡ ከእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው የተነሣ፡ በዚያ ብቅዓታቸውና ዕድሜያቸው የወለዱት፣ የካህኑ ዘካርያስና የአክስቴ ኤልሣቤጥ፡ አንድ ወንድ ልጃቸው የኾነው፣ እኔም፡ ልጄን ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በቤተ-ልሔም በረት፡ በወለድሁት ጊዜ፡ ገና የስድስት ወር ጨቅላ ሕፃን የነበረው፥ አድጎ፡ ነፍስ ካወቀ በኋላም ወደበረሃ ገብቶ፡ በፍጹም ብሕትውና ኖሮ ሲያበቃ፣ በመጨረሻ፡ የልጄንና የወዳጄን እውነተኛ ማንነት፡ ለመጀመሪያ ጊዜ መስክሮ፡ በውኃ ጥምቀቱ፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ በይፋ ያሳወቀው፡ <u>**መጥምቁ ዮሓንስ**</u> ነው።

እናንተ የማታስተውሉ ደካሞች! ገና፡ "ቀውስጦስ"፡ የሚለውን ስም፡ ስትሰሙ፥ ወይም ስታውቁ፡ እንዴት፡ ጥርጣሬው እንኳ ሳያድርባችሁ ቀረ? እንደእነርሱ፡ እንደሓሳውያኑ ስለኾናችሁ አይደለምን? አዎን! በመኾናችሁ ነው እንጂ።

አለዚያማ፡ እኔ፡ ራሴ፡ በዚህ፡ የዐዋጅ ቃሌ፡ እስክገልጠው፣ እስከዛሬው ድረስ፡ ይህንኑ ሓሳዊ ይትበሃል፡ለዚህን ያህል ዘመን፣ ይኸው ዝም ብላችሁ ተቀብላችትና አምናችሁበት እንዴት ልትኖሩ ይቻላችሁ ነበር? ፈጽሞ፡ አይቻላችሁም ነበር።

ለመኾኑ፡ የእኛን፡ የእግዚአብሔርን ቅዱሳት መላእክት ስሞች፡ ለይታችሁ ያወቃችሁበት አጠራር፡ ከነትርጉሙ፡ ይኼ ኖርዋልን? አይደለም። የአንጋደ መላእክቶቻችንና የእነርሱ አለቆች የኾኑት፡ የቅዱስ ሚካ-ኤል እና የቅዱስ ገብር-ኤል፣ የቅዱስ ዑራ-ኤል እና የቅዱስ ሩፋ-ኤል፣ የቅዱስ ራጉ-ኤል እና የቅዱስ ፋኑ-ኤል፣ በዐርባዕቱ እንስሳት ስምና መልክ የሚታወቁት፡ የመንበረ-ጸባዖታችን ተሸካሚዎችና ጠባቂዎች የኾኑት ሱራፍ-ኤል እና ኪሩብ-ኤል፣ የሌሎቹም ኹሉ፡ ስማቸው፣ እንዲያውም፡ በቀዳሚው የፍጥረት ጊዜ፡ ለእነዚህ ሊቃነ-መላእክቶቻችን ኹሉ፡ የበላይ አድርገን የሾምነው፣ እስከዛሬም፡ መጠሪያውን ለውጦና ተቃዋሚያችን ኾኖ፡ በዚያው ፀረኝነቱና ክፋቱ፣ ሓሳዊነቱና ጥፋቱ የቀጠለው፡ ዲያብሎስ እንኳ ሳይቀር፡ "የእግዚአብሔር-ተፃራሪ" የሚል ትርጉም ያለው፣ "ሳጥና-ኤል" የሚለው ስሙ፡ "ኤል" የሚለውን፡ የእኛን፡ እግዚአብሔራዊ የተቀደሰ መታወቂያ ቃል መደብ ያደረገ መኾኑን፡ አዎን! አበክራችሁ ታውቃላችሁ።

ይህ ብቻ አይደለም፤ "የእግዚአብሔር ልጆች" እና "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት ኪዳናውያን እና ኪዳናውያት ታማኞቻችን፡ በግእዙ እና በኢትዮጵያኛው ልሳናችን፡ "ሚ"፡ መኑ፣ ወይም፡ ማን፣ "ካ"፡ ከመ፣ ወይም፡ እንደ፣ "ኤል"፡ እግዚአብሔር አብወእም፤ እንዲሁም፡ "ገብር"፣ አገልጋይ፣ "ኤል"፡ እግዚአብሔር አብወእም፤ የሚል ትርጉም ያላቸውን ስያሜዎች መኾናቸውን ታውቃላችሁ።

ከዚህ የተነሣ፡ ለሊቃነ መላእክቶቻችን፡ ፩ኛ፡ "እንደእግዚአብሔር አብወእም፡ እውነተኛ አምላክ፡ ማን አለ?" የሚለውን፡ ለ"ሚካኤል"፣ የእግዚአብሔር አብወእም አገልጋይ!" የሚለውን ደግሞ፡ ለ"ገብርኤል" በመስጠት፡ እናንተም፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ባገኛችሁት የስያሜ ሥርዓት፡ "ስምን፡ መልአክ ያወጣዋል!" እያላችሁ፡ በምትሰይሙት ባህላችሁ፡ ራሱን፡ "'ቀውስጦስ' እባላለሁ!" ብሎ፡ እውነተኛ ስሙን ባስታወቀበት፡ በመጀመሪያው ጊዜ፥ በዚህ ረገድ፡ እንዴት፡ አንዳችም ጥያቄ አላቀረባችሁም?

ኋላም፡ ይኸው ሓሳዊ ይትበሃል፡ በግብፅ ኦርቶዶክስ መነኮሳትና ጳጳሳት አማካይነት፡ እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" ብላችሁ ለምትጠሩ፡ የሰው ወገኖች ሲደርሳችሁ፡ "ይህ፡ በእግዚአብሔሩ ሥርዓታችንና ትውፊታችን፡ ሰምተነው የማናውቀው፣ ይልቁንም፡ ግልጽ ከኾነው፡ ከተልእኮው ድርጊት ሰይጣናዊነት በላይ፡ ራሱ፡ ስመ-መልአኩ፡ እንግዳ አጠራር ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔራዊም ባለመኾኑ፡ እስኪ እንመራመረው!" እንኳ አላላችሁም።

የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም፡ ባዕዳን ገዢዎቻችሁ ኾነው፡ በቀደምትነት ለመጡት፡ ለኦሪታውያኑ አይሁድ እንዳደረጋችሁት ኹሉ፤ ኋላ፡ በመከታተል የመጡባችሁ፡ አዲሶቹ ኦርቶዶክሳውያኑን ግብፆች መነኮሳት ጳጳሳት፡ ያመጡባችሁን፡ ሓሳዊ ይትበሃል፡ አዎን! "እሺ! እናጣራው!" ብላችሁ እንኳ ሳታስቡ፡ እንዲያው፡ በጭፍን ብቻ፡ ዝም ብላችሁ እንደተቀበላችሁት፡ ይኸው ግብራችሁ መሰከረባችሁ።

እንዲያማ ባይኾን ኖሮ፡ ሌላው ቢቀር፡ በእግዚአብሔራዊው ሥርዓታችን፡ ከምስጢርነት ይልቅ ጎልቶ የሚናገረውን፡ "'ቀውስጦስ' የሚለውን የቃለ-ስያሜውን እስኪ! እንመልከተው ባላችሁ ነበር። ነገር ግን፡ ቀላልና ግልጽ የኾነውን ይህን ሙከራ እንኳ አላደረጋችሁም፤ "ስምን መልአክ ያወጣዋል!" በሚለው እግዚአብሔራዊ ባህላችሁም፡የስሙ ሰይጣናዊ ማንነትና ምንነት ግልጽና ቀላል መኾኑ፡ በገሃድ እየታየ እና እየታወቀ፤ ይህ እውነታ፡ እኔ ራሴ፡ ይኸው አኹን እስክገልጠው ድረስ፡ እስከዛሬ ሳይከሠትና ሳይጋለጥ መቆየቱ፡ በሰዎች ዘንድ፣ በእናንተ ዘንድ ጭምር፡ **የእኛ፡ የእግዚአብሔር ከኾነው፡ ከመልካሙ ይልቅ፡** *የዲያብሎስ የኾነው፡ የክፋቱ ኃይል፡* የቱን ያህል ተቀባይነትን አግኝቶ ያየለ መኾኑን፡ ያለአንዳች ጥርጣሬ ያረጋግጣል።

ይኸውም፡- ግእዝ ባስገኘው ኢትዮጵያኛ ልሳን፡ *"ቀውስ"፣ ቀውስ ነው፤ "ጦስ"ም፡ ጦስ ነው፤ ስለዚህ፡ "ቀውስጦስ"፡ ቀውስን እንዲያስከትል፡ ጦሰኛ ኾኖ፡ ከአለቃው፡ ከዲያብሎስ የሚላክ፡ ርኩስ-መንፈስ፣ ጋኔን፣ ሰይጣን ነው!"* ማለት ነው።

እንግዴህ፡ ይኼን እውነታ እያወቃችሁ ነው፡ በተፈጥሮአቸው፡ ንጽሓ-ጠባይን የተሸለሙና በዚያ የተጌጡ ከመኾናቸው በቀር፡ ምንም ኃጢአት የሌለባቸውን፣ ሊገኝባቸውም የማይቻለውን፡ ሕፃናት ፍጡሮቻችንን፡ በሰይፋቸው እየቀሉ እንዲገድሉ፡ እኛ እግዚአብሔር መላእክቶቻችንን አዝዘን እንደላክን ተደርጎ የቀረበላችሁን የሓሰት ተረት ተቀብላችሁና አምናችሁ የኖራችሁት።

እነዚህ ሕፃናት እኮ፡ መልካችን ብቻ ሳይኾኑ፣ ከእኛም፡ እንደአንዳችን አድርገን፡ በወንድነትና በሴትነት ፈጥረን፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስም ወልደን፣ ፍጡሮቻችን ብቻ ሳይኾኑ፡ ለታማኙ ኢትዮጵያዊው አገልጋያችን፡ ለመልከ-ጼዴቅ በሰጠነው በቅዱሱ-ኪዳናችንም፡ ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ኾነው፡ በእኔ ምሥዋዐ-መድኃኒትነትና፡ በልጄ፡ በወዳጄ፡ ሰላመ-መስቀል ቤዛነት፡ ተመልሶ የተገኘውን፡ መልካሙን የገነት ሕይወት፡ በፍጹም ብቅዓት ይኖሩት ዘንድ፡ ወደዚች ምድር የላክናቸው ናቸው።

አዎን! እንዲህ ያሉትን፡ ሕፃናቶቻችንን፡ በሰይፋቸው እየቀሠፉ እንዲያርዱ፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ታዝዘው እንደተላኩ ተደርጎ፡ ተቀባይነትንና ተአማኒነትን ያገኙትን የዲያብሎስን "መልእክተኞች" ነው፣ "እውነተኞቹ፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር ቅዱሳት መላእክት ናቸው!" ብላችሁ፡ ስታወድሷቸው፣ ከእነርሱም መካከል፡ በአዲሱ መልአካዊ ስሙ ሳይኾን፥ "ቀውስጦስ" በተባለው፡ በቀደመው ሰይጣናዊ ስሙ፡ ስትጠሩበትና ስትሾሙበት የኖራችሁት፣ አኹንም፡ እየኖራችሁበት ያላችሁት!?

ታዲያ! በዚህ ክፉ ግብራችሁ፡ እንዲህ፡ እጅ ከፍንጅ ተይዛችሁ ከምትገኙት፡ ከእናንተ፡ ምን ቍም-ነገር ሊጠበቅ ይቻላል? አይቻልም።

ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ምንም ዓይነት በደል ሳይኖርበት፡ እየራሳቸውን ወደሰይጣንነት የለወጡ፡ እናንተን የመሰሉ፡ ክፉዎች አይሁዳውያን ሰዎች፡ ያን የሚያህል አሠቃቂ መከራንና ሥቃይን በሚፈጽሙበት ጊዜ፡ "አባ ሥረይ ሎሙ! እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ!

አባቴ ሆይ! እኒህ ጨካኞች፡ ከሚጠቅማቸው፡ ከመልካሙ ኹሉ ብቻ በቀር፡ አንዲት ትንሽ በደል እንኳ ባላደረግሁባቸው፡ በእኔ ላይ፡ ይኸው እየፈጸሙ ያሉትን፡ ይህን የሚያህለውን ከባዱን ግፋቸውን፡ ይቅር በላቸው!" ብሎ፡ ራሱ፡ በሰውነቱ፡ ይቅርታ ጠያቂ፤ በመለኮትነቱም፡ በራሱ፡ ይቅር ባይ ኾኖ፡ ምሕረትን ባስገኘላቸው፡ በዚያ እግዚአብሔርነታችን ላይ፡ ያንኑ ግፋቸውን፡ በተጠናከረ ይዘት የቀጠሉት አሪታውያኑ የአይሁድ ካህናትና ሊቃነ-ካህናት፤ አርቶዶክሳውያኑም የግብፅ መነኮሳትና ጳጳሳት ያቀረቡላችሁን፡ እጅግ የከፋውን ግዙፉን ሓሰት፡ እንደእውነት የተቀበላችሁ፤ ለዝንተ-ዓለምም ስታስተናግዱ የኖራችሁ፡ እናንተ፡ ይህን፡ ቀላሉንና ገሃዱን፡ "'ቀውስጦስ' የሚለው ስም፡ የባዕዱ የዲያብሎስ እንጂ፡ የቅዱሳቱ የእኛ የእግዚአብሔር መላእክት ሊኾን አይችልም!" ብላችሁ፤ አመዛዝናችሁና አስተውላችሁ፡ ትክክለኛውንና እውነተኛውን ውሳኔ፡ ከቶ፡እንዴት ልትሰጡ ይቻላችኋል? አይቻላችሁም። (ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬።)

እንዲህ፡ በግልጽ የምወቅሳችሁና የምነቅፋችሁ፤ የምገሥፃችሁና የምዘልፋችሁ፡ እስከመጨረሻው የምወድዳችሁ ልጆቼ ስለኾናችሁ ነውና፡ ደስ ይበላችሁ! በእግዝእተብሔርነቴ እውነትና መንፈስ የምናገረውና እናንተም የምትሰሙት፡ ይህ የምእዳን ቃሌ፡ አምናችሁበት ብትፈጽሙት፡ ለሥጋችሁና ለመንፈሳችሁ፤ ለነፍሳችሁና ለኹለንተና ሕይወታችሁ፡ ይበጃችኋልና፡ ደስ ይበላችሁ!

የክፋት አገልጋይ ኾኖ የኖረውን፤ እንግዴህ ወዲህ ግን፡ ለሌሎቹ መሰሎቹ ርኩሳን መናፍስት ብቻ ሳይኾን፤ ለዓመፀኞች ሰዎችም ኹሉ ጭምር፡ የሚያበራ ተስፋና የአብነት አርአያ የሚኾነውን፡ "ቀውስጦስ" የተባለውን፡ የዚህን ሰማያዊ ፍጡር፡ እጅግ መልካምና አስደናቂ ፍጻሜ፡ ከዚህ አከታትዬ፡ በእኔው አንደበት ስለማሰማችሁ ተዘጋጁ! እርሱም፡ ይኸውላችሁ!

አዎን! ጃንደረባው አገልጋዬ ዮሴፍና ረዳቴ ዘመዴ ሰሎሜ፡ ሕፃን ልጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን ይዤ፡ ወደግብፅ በምንጓዝበት፡ የስደት መንገዳችን ላይ እያለን፡ ለጊዜው ዐርፈንባት ባለች፡ በአንዲት ቅድስት ደብር ዓጸድ ውስጥ ወድቆ የነበረውን "ቀውስጦስ"ን አገኘነው።

ያችም፡ ቅድስት ደብር፡ በሓሳውያኑ የታሪክ መጽሓፍ፡ *"ቀውስጦስ፡ መልከ-መልካም ሕፃን፡ ከነማርዳው አገኘ። 'ለዝሰ፡ ዘፈጠሮ ይቅትሎ! ይህንስ፡ የፈጠረው ይግደለው!' ብሎ ትቶታል። የቀሩት መላእክት፡ የተላኩበትን ፈጽመው ሲያርጉ፤ እርሱ፡ ኃይል ተነሥቶት ቀረ። አሻግሮ ቢያይ፡ በደብረ-ቀልሞን፡ ዐምደ-ብርሃን ተተክሎ አየ። 'ዛቲ መካን፡ ትከውነኒ አራቂተ፡ ምስለ እግዚእየ! ከፈጣሪዬ እግዚአብሔር ጋር የምታስታርቀኝ፡ ይህቺ ቦታ ናት!' ብሎ፡ ተጎትቶ ኼዶ፤ ከደጇ ብርሃኗ ወደቀ።"* የተባለችው መኾኗ ነው።

ከእኛ ከእግዚአብሔር በተሰጠው፡ ማዕርግና ሥልጣን፡ ርእሰ-ሊቃነ መላእክት የነበረው *"ሳጥናኤል"*፡ በእኛ ላይ ዓምፆ፡ ታላቁን ክህደት በፈጸመ ጊዜ፡ በክፉ ግብሩ ተዋርዶ፤ ከሰማይ፡ ወደምድር ሲጣል፡ "ዲያብሎስ" እንደተባለ ኹሉ፤ መልአከ-እግዚአብሔር የነበረው ጎሩዬል [ጎሩየ-ኤል]ም፡ የዚሁ የዲያብሎስ ዐባሪዎቹና ተባባሪዎቹ ኾነው ከተከተሉት መላእክት መካከል፡ አንዱ ኾኖ በመገኘቱ፤ በጥንተ-ተፈጥሮው፡ በእኛ፡ በተቀደሰበት፡ የእግዚአብሔር መልአክነቱ ባሕርይ፤ ከእኛ ባገኘው፡ የምርጫ ነጻነቱ ተጠቅሞ፡ በራሱ ፈቃድና ፍላጎት፡ ራሱን፡ ወደርኩስ መንፈስነት ለውጦ ስላዋረደ፤ እርሱም፡ እንደመሪው፡ እንደዲያብሎስ፡ ስሙ፡ "**ቀውስጦስ**" በሚለው አጠራር ተቀይሮ እንዲተካ ኾነ።

ይህ ቀውስጦስ፡ የካህኑ ዘካርያስና የአክስቴ የኤልሣቤጥ ልጅ ለኾነው፡ ለፊተኛው ሕፃን፥ ለኋለኛውም፡ መጥምቁ ዮሓንስ፡ ባደረገው፡ እግዚአብሔራዊ ርኅራኄ ምክንያት፡ አለቃው ዲያብሎስ፡ እጅግ ተቆጥቶ ያደረሰበትን ብርቱ ጥቃት በመቃወምና በመቋቋም፡ እስከዚያች አፍታ ድረስ ሲፈጽመው በኖረው ተመሳሳይ ሰይጣናዊ የጭካኔና የግፍ ሥራው፡ እጅግ ተጸጽቶ፡ በእኛ በእግዚአብሔር ፊት፡ በፍጹሙ ንስሓ ጸድቆ በመታየቱ፡ እግዚአብሔር አብ እና እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፥ ደግሞም፡ ሕፃኑ ልጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ እና ሕይወታችን፡እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ፤ ከቅዱሳት መላእክቶቻችንና ሊቃነ-መላእክቶቻችን ጋር፡ ኹላችንም በአንድነት በተገኘንበት መለኮታዊ አደባባይ ላይ፡ ኃጢአቱንና በደሉን ኹሉ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ይቅር ብለነው፤ ስሙንም፡ "ጎሩዬል = ጎሩየ-ኤል" ተብሎ ይጠራበት ወደነበረው፤ ወደቀደመው መልአካዊ ስሙ መልሰን፤ በዚያ ስሙ እየተጠራ እና በመላእክት ማኅሌት እየተወደሰ፡ ባጎናጸፍነው፡ በእግዚአብሔርነታችን የብርሃን ክብር ተሸልሞ እና የድል አክሊልን ተቀዳጅቶ፡ እዚያው እያየነው፡ በቅዱሳት መላእክት ጓደኞቹ ታጅቦ፡ በይባቤ፡ ወደሰማያት ዐረገ።

በዚህ ጊዜ፡ በምድርም፤ በሰማይም ታላቅ ሓሤት ተደረገ! ኾነም።

እኛም፡ የስደት መንገደኞቹ፡ የጥድፊያ ጉዟችንን፡ በደስታ ተመልተን፡ ቀጠልን። (ሉቃ. ፲፰፥ ፩-፲።)

ይህ ነው፡ ትክክለኛው እና እውነተኛው፡ የቀውስጦስ ዝክረ-ነገር።

# ታላቅ የምሥራች ዜና!

ከዚህ ጋር የተያያዘ፡ ታላቅ የምሥራች ዜና ስላለኝ፡ ይህንኑ ምሥራች፡ እዚህ ላይ! እኔው ራሴ፡ በመለኮታዊው የትስብእት ቃሌ፡ "የምሥራች!" ብዬ አበሥራችኋለሁ።

እናንተም፡ "ስለምኑ ነው የምታበሥሪን!" እንደምትሉኝ ዐውቃለሁ። የምሰጣችሁ መልስ፡ ይህ ነው፦

ነቢያትንና ሓዋርያትን፣ ጻድቃንንና ሰማዕታትን፣ እነክርስቶስ-ሠምራንን የሚያጠቃልለው፡ መላው የነፍስና የሥጋ፣ የመንፈስም ፍጥረታችን ጉባኤ የኾናችሁት፡ ኹላችሁ ልጆቻችን ሆይ! አዎን! እንግዴህ፡ እጅግ ደስ ይበላችሁ!

እነሆ፡ በራሱ ምርጫና በገዛ ፈቃዱ፡ ራሱን፡ ወደርኩስ መንፈስነት አዋርዶና ወደክፉ አገልጋይነት ለውጦ፡ "ቀውስጦስ" በሚለው ሰይጣናዊ ስሙ፡ ራሱ፡ ሲማስን፣ ሌላውንም፡ ሲያማስን የኖረው፡ የቀደመው መልአካችን ጎሩዬል [ጎሩየኤል]፡ ዛሬ ያንኑ ራሱን፡ በእውነተኛ ሃይማኖቱና በበጎ ምግባሩ፡ ለፍጹሙ ንስሓ በማብቃቱ፡ በዚያው፡ በቀዳሚ ስሙ፡ ወደጥንተ-ተፈጥሮውና የቅድስና ህልውናው እንደተመለሰ፡ ይኸው፡ ከእኔው አንደበት፣ በእኔው የዐዋጅ ቃሌ፡ እነሆ ሰማችሁት።

እንደዚሁ ኹሉ፣ ለፍጥረታተ-ዓለማታችን ጠቅላላ ጉዳትና ጥፋት፡ ዐቢይ ምንጬና ቀዳሚ መነሻው፣ መሪው አበጋዝና አስፈጻሚው ባለቤት የኾነው ዲያብሎስም፡ ከነሠራዊቱ፡ ራሱን፡ በንስሓ አንጽቶና አጽድቆ፡ ወደቀደመው መልአካዊ ጥንተ-ተፈጥሮው ይመለሳል።

በዚያን ጊዜም፡ እውን ግህደቶች በኾኑት፡ በመልካምነት እና በእውነት፣ በሕይወት እና በሕያውነት መሥርተን የፈጠርናቸው፡ መላው፡ የሰማይና የምድር፣ መንፈሳውያት እና ሥጋውያት ዓለማታችን፡ የምትሓት ክሥተቶች ኾነው፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ሲያማስኗቸው ከኖሩት፡ ከክፋት እና ከሓሰት፣ ከሞት እና ከጥፋት፡ ፍጹም ነጻ ኾነው፣ ሲዖልና ገሃነመ እሳትም ሳይቀሩ ተዘግተው፡ እነዚህ፡ የዲያብሎስ ግብሮችና ጠንቆቻቸው ኹሉ፡ ተጠቃልለው፡ ወደኅበ አልቦነታቸው [ወደአለመኖርነታቸው] ይመለሳሉ።

እነዚያ፡ በመልካምነት እና በእውነት፣ በሕይወት እና በሕያውነት መሥርተን የፈጠርናቸው፡ መላው፡ የሰማይና የምድር፣ መንፈሳውያት እና ሥጋውያት ዓለማታችን ደግሞ፡ ወደቀደመው፡ ወደኅበ ቦነታቸው [ወደመኖርነታቸው] ተመልሰው፡ በዘለዓለማዊው ነዋሪነታቸው ጥንተ-ተፈጥሮአቸው ይገለጣሉ።

ይህን እግዚአብሔራዊ እውነታችንን፡ እነሆ፡ አኹንም፡ እኔው ራሴ፡ በመለኮታዊው እና በትስብእታዊው አንደበቴ፡ አረጋግጬ፡ ይኸው ነገርኋችሁ። አሳወቅኋችሁምም። ስለዚህ፡ ደስ ይበላችሁ!

እስካኹን፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ጸንቶ እና ቀጥሎ የቆየው፡ የእነዚህ፡ የእውንና የምትሓት አኗኗሮች የቅጥ ኹኔታ ዐብቅቶ፡ በፍጻሜው፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ ወደጥንተ ተፈጥሮ ህልውናቸው፡ የመመለሳቸው፡ ይህ ዕፁብ ድንቅ ምስጢራዊ ነገር፡ እንግዴህ፡ ይኸው፡ እንዲህ ተከሠተላችሁ አይደለም? አዎን! ተከሠተላችሁ። በዚህም፡ አኹንም እላችኋለሁ፤ እጅግ ደስ ይበላችሁ! የተከሠተላችሁም፡ በእውነተኛውና በትክክለኛው የቀውስጦስ ዝክረ-ነገር ነው።

ይኸውም፡ ከመጀመሪያው እስካኹን፡ ለዝንተ-ዓለም የቀጠሉት፡ እነዚህ ኹሉ፡ የእውንና የምትሓት ክሥተቶችና አኗኗሮች፡ በአጠቃላዩና በመጨረሻው እውነተኛ ንስሓ፡ በንጽሓ-ባሕርዩ፡ ፍጹም መልካም ወደኾነው፡ ወደቀደመው እግዚአብሔራዊው ጥንተ ህልውናቸውና ሕይወታቸው፡ እንዴት የሚመለሱ ለመኾናቸው፡ ይህ፡ የመልአኩ፡ የኀሩዬል እና የሰይጣኑ፡ የቀውስጦስ ተፃራሪና ተነጻጻሪ ኾኖ የቀረበላችሁ ዝክረ-ነገር፡ በሚበቃ አብራርቶና አጕልቶ፣ አሟልቶና አረጋግጦ ያስገነዘባችኋል።

አዎን! በጥንተ-ንጽሕናና ቅድስና የተፈጥሮው ከኾነው፡ ከእውነተኛው መልአካዊ አካሉና ባሕርዩ፡ በራሱ ነጻ ፈቃድና ምርጫ፡ ራሱን፡ ከኀሩይ-ኤል ማንነቱ፣ ኢተፈጥሮአዊና ሓሳዊ፥ ሰይጣናዊም ወደኾነው፣ ወደድኅረ-አብሶና ርኵሰት፡ በራሱ ነጻ ፈቃድና ምርጫ፡ ራሱን፡ ወደዚያ ወደቀውስጦስነት ምንነት፡ ለውጦ እንደነበረ ኹሉ፥ አኹን ደግሞ፡ እንደገና፡ ያው አንዱ ቀውስጦስ፡ በዚያው፡ በራሱ ነጻ ፈቃድና ምርጫ፡ የዚያ ምንነቱ አካልና ባሕርይ የኾነ፡ ያንኑ ራሱን፡ ከዚሁ ኢተፈጥሮአዊና ሓሳዊ፥ ሰይጣናዊም ከኾነው፣ ከድኅረ-አብሶውና ርኵሰቱ፡ በአማናዊው ፍጹም ንስሓው አጽድቆና አድሶ፡ ለዚያው፡ በጥንተ-ንጽሕናና ቅድስና የተፈጥሮው ለኾነው፡ ለእውነተኛው መልአካዊ አካሉና ባሕርዩ፡ በዚያው፡ በራሱ ነጻ ፈቃድና ምርጫ፡ ራሱን፡ ለዚያው፡ ለቀደመው የኀሩየ-ኤል ማንነቱ መልሶ ለማብቃት መቻሉን፡ አረጋግጦ አሳየ፤ አሳወቀም።

በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ-መድኃኒትነትና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የመስቀለ-ሰላም ቤዛነትም፡ የምትሓትና የሰይጣን የኾኑት፡ ክፋት እና ሓሰት፣ ለአንዴ እና ለዘለዓለም፡ ወደአለመኖርነታቸው እንደተመለሱ ኹሉ፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ በመስቀል ሞታች እና በሙታን ትንሣኤያችን፡ እየራሳቸውን፡ በገዛ ፈቃዳቸውና ምርጫቸው፡ ለሞት እና ለጥፋት በማስገዛታቸው፡ ከመጀመሪያዎቹ አዳም እና ሔዋን አንሥተው፡ እስከዚህ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር ሕይወት እና ሕያውነት የተለዩት፡ የሞት ባለዕዳዎች እና የጥፋት እስረኞች ኾነው የሚሠቃዩ ኹሉ፡ ከዚሁ ከሞት ባለዕዳነታቸው እና ከጥፋት እስረኝነታቸው፡ ነጻ ኾነው ተለቅቀውና ተነሥተው፡ የዘለዓለምን ሕይወት ስለሚወርሱ፡ ሞት እና ጥፋትም፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ ወደአለመኖርነታቸው ይመለሳሉ።

በዚህ ጊዜ፡ በታማኙ ጽኑ ሓዋርያችን፡ በጳውሎስ እንደተጻፈ፡ "እሜሃ ይከውን ማኅለቅትሰ፤ አመ ተወፈየ እግዚአብሔር አብ፡ መንግሥቶ [እምወልደ እግዚአብሔር፡ ኢየሱስ መሲሕ]፤ ወአመ ተሰዐረ፡ ኵሉ መኰንን፤ ወኵሉ ንጉሥ፤ ወኵሉ ኃይል።

"ልጄ-ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ መንግሥቱን፡ ለአባቱ እና ለእኔ መልሶ ባስረከበ ጊዜ፣ የዓለሙ ገዢ ኹሉ፣ ንጉሥ ኹሉ፣ ኃይል ኹሉ፡ በተሻረ ጊዜ፡ በዚያን ጊዜ፡ አኹን ያለው፡ የዚህ ዓለም የማሰነ ሥርዓት ፍጻሜ ይኾናል።

"ወእምዝ ይሰዐር፡ ደኃሪ ጸላኢ፣ ዘውእቱ ሞት፤ እንዘሂ ያገርር ኵሎ፡ ታሕተ እገሪሁ።

"ከዚህ በኋላ፡ ኹሉን፡ ከእግሩ በታች አድርጎ ያስገዛው፣ የመጨረሻው ጠላት፡ እርሱም፡ ሞት፣ ይሻራል።" (፩ኛቆሮ. ፲፭፥ ፳፬-፳፮።)

## መፈጸም።

አገልጋይ ልጃችን፡ ኤርምያስ፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ፡ እስካኹንም ቢኾን፡ ትምህርቱንና ዕውቀቱን ኹሉ ያገኘውና የሚያገኘው፣ እኛ እግዚአብሔር፡ በማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡራችን፣ በሴቷም ኾነ በወንዱ ልቦና ውስጥ፡ በተፈጥሮ በጻፍነው መጽሓፋችን ላይ እንዳደረግነው እና እንደምናደርገው፡ እርሱም፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ፡ ከእኛ እየተገለጠለት የሚቀርብለትን እንጂ፡ ከሰዎች በተማረው አይደለም። ከዚህ የተነሣ፡ ሰዎች የጻፏቸውን መጻሕፍት አያነብብም።

እኛ እግዚአብሔር፡ በልቦናው ውስጥ ያለውን ኹሉ የምናውቀው ቢኾንም፡ በዚህ ረገድ፡ ለእርሱ፡ በቀጥታ፡ በመንፈስ ለምናቀርብለት ጥያቄ፡ የሚሰጠን መልስ፡ በተለይ ለእናንተ፡ ለልጆቻችን ኹሉ፡ የሚጠቅማችሁ ኾኖ ስላገኘነው፡ "ሰዎች የጻፏቸውን መጻሕፍት፡ ለምን አታነብባቸውም!" ብለን፣ በተለይ፡ በእኔ ቃል ጠየቅሁት።

እርሱም! "በፍቅርሽ ሞቼ፡ ሕያው የኾንሁ፡ ቅድስት እናቴ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ሆይ? ይህን ጥያቄ፡ ከመለኮታዊው እና ከትስብእታዊው ቃልሽ፡ በእውነተኛው የመንፈስ-ቅዱስ አምልኮቱ፡ እንድሰማው በማድረግሽ፡ 'ትሑት አገልጋይሽ!' ልባል እንኳ የማይገባኝ፡ እኔ፡ ይህን የሚያህል ክብር አገኘ ዘንድ፡ እኔ ማነኝ?" ብሎ፡ በፊቴ ከሰገደ በኋላ፡ ተነሥቶና ቆሞ፡ እንዲህ የሚለውን አጭር መልሱን ሰጠኝ፡- ያም ይኼውላችሁ! ስሙት!

"ሰዎች፡ ኹሉንም መጻሕፍት፡ 'ቅዱሳት እና መንፈሳውያት ናቸው!' የሚባሉትን ጭምር፣ ከእነርሱ አስቀድመው የነበሩና እነርሱን የመሰሉ ሰዎች፡ በዚያው፡ ሕፁፅ [ጐደሎ] ከኾነው፡ ከሰብአዊው አእምሮአቸው አንቅተው ያሰቧቸውን፣ በአንደበታቸው የተናገሯቸውንና በብዕራቸው የጻፏቸውን ቃላት ብቻ፡ መሠረትና መነሻ፣ ምስክርና ማስረጃ በማድረግ ስለሚጽፏቸው፣ ወይም ደግሞ፡ ድርሰቶቻቸው ኹሉ፡ በሰዎች የትምህርትና የዕውቀት ሥርዓት እንጂ፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ፥ ዕውቀትና እምነት፣ ስም-አጠራርም ላይ የተመሠረቱ ኾነው የሚጻፉ ባለመኾናቸው፥ ፍጹም የኾነውንም የእግዚአብሔርን እውነት ስለማይናገሩ ነው! የማላነብባቸው።

"እኔ የማነብበው፣ 'ፍጹም እውነት ነው!' ብዬም፡ በሃይማኖት የምቀበለው፣ ከዚህ የተነሣም፡ በምግባር የምፈጽመው እና ሕይወት አድርጌ የምኖረው፡ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ፡ በውስጤ ያኖረውን፣ የጻፈውንና የገለጠልኝን ብቻ ነው። እኔ ራሴ፡ እግዚአብሔር የጻፈኝ መጽሓፉ ስለኾንሁ፡ በአእምሮዬ የማስበው እና በአንደበቴ የምናገረው፣ በጽሑፍ የምገልጸው እና በሥራ ላይ የማውለው፡ ያን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ብቻ ነው።

"ከሰው፡ የማየውንና የምሰማውን፣ የማነብበውንም፣ 'የእግዚአብሔር እውነት እና ትክክል ነው!' ብዬ የምቀበለው፡ እግዚአብሔር፡ ገና በማሕፀን ሲፈጥረኝ፡ በተፈጥሮ፡ በውስጤ ካኖረው፣ ከጻፈውና ከገለጠልኝ ጋር የተስማማ፣ ወይም፡ አንድ ኾኖ ሳገኘው ብቻ ነው። ምክንያቱም፡ የመንፈስ ቅዱስ እውነት እና ዕውቀት፡ አንድ እና አንድ ብቻ ስለኾነ ነው።

**"'ዕወዲ ሕግየ ውስተ ኅሊናሆሙ። ወእጽሕፎ ውስተ ልቦሙ። ወኢይምህር እንከ እኁ፡ እኅዋሁ፡ እንዘ ይብል፡- ‹አእምርዎ ለእግዚአብሔር!› እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፣ ንኡሶሙ፣ ወዐቢዮሙ።**

"'ሕጌን፡ በእያንዳንዳቸው መንፈስ ውስጥ አኖራለሁ። በነፍሳቸውም ላይ እጽፈዋለሁ። ስለዚህ፡ አንዱ ሰው፡ ሌሎቹን መሰሎቹን ሰዎች፡ ‹እግዚአብሔርን ዕወቁ!› ብሎ አያስተምርም። ትንንሾች ልጆችም፣ ትልልቆች አዛውንቶችም፣ ኹሉም ያውቁኛልና።' የሚለው የእግዚአብሔር ቃል፡ በዚህ ረገድ ላለኝ እምነቴና ምግባሬ መሠረት ነው። " አለን። (ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬። ዕብ. ፰፥ ፰-፲፪፣ ፲፥ ፲፭-፲፮።)

ስለዚህ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ይህን ውሳጣዊ እምነቱንና አስተሳሰቡን ስለምናውቅ፣ እስካኹን ያነበባቸው መጻሕፍት፣ ወይም፡ "ቅዱሳት መጻሕፍት" በምትሏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያሉትን ቍም-ነገሮች ኹሉ እንኳ እንዲያስተውላቸው፣ መጻሕፍቱም፡ በሰዎች አማካይነት እንዲደርሱት፣ ወይም እንዲያገኛቸውም እያደረግን ያቀረብንለት ብቻ መኾናቸውን እናውቃለን።

አኹንም፡ ስማቸውን፡ ቀደም ብዬ የጠቀስኋቸውን መጻሕፍት እንዲደርሱትና እንዲመለከታችው ያደረግን እኛ ነን።

ለዚህ ተልእኮ አዘጋጀተን የጠራነው፣ እርሱም፡ ጥሪያችንን ተቀብሎ እየሠራ ያለው፡ በቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ኢትዮጵያዊነት እና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አገልግሎቱ ገድል ጸንቶ፡ እንደጀግና አርበኛና እንደቆራጥ ተጋዳይ፣ በኢትዮጵያው ስሜ ለተጠራው ትውልድ፡ ኪዳናዊ አገልግሎቱን ያበረክት ዘንድ፡ በስጦታነቱ፡ "ሀብተ-ማርያም" ብዬ የሰየምኩት፡ ልጄና ካህኔ ዘርፉ፣ ቀደም ብሎ፡ ሌሎች መጻሕፍትን በማቅረብ፡ በየጊዜው ሲያደርግለት እንደቆየው ኹሉ፡ አኹንም፡ ይህን፡ "ገድለ-አዳም" የተባለውን መጽሐፍ፡ ለኤርምያስ እንዲያቀርብለት ያደረግነው እኛ ነን።

ከኪዳናዊው ልጄ እና አገልጋዬ ሀብተማርያም ጋር፡ በዚህ ኹሉ የአገልግሎት ዘርፍ፡ ስለእኔ፡ ስለቃል-ኪዳን እናታቸው ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም እና ስለእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ዛሬም፣ ወደፊትም፡ በብቅዓት ለሚመሰክሩ ታማኞች ልጆቹ ኹሉ፡ ድምፁ ሳይሰማ፡ በኅቡዕ፡ ዘውድ ኾኖ እየተጋደለ ያለው፡ የመጨረሻው ተከታታይ ወንድሙ፡ አክሊለ ሰማዕት ይገኛል።

በሥጋዊው የሕክምና ትምህርትና ዕውቀት፡ ለመጨረሻው የሊቀ-ምሁርነት ማዕርግ በቅተው፡ "ሓኪም ዘርፉ" እና "ሓኪም አክሊሉ" የተባሉት፡ እኒህ ኹለት ወንድማማች ልጆቻችን፡ ከትልቅዬው ሚስት፡ ከሡናይት አርአያ፣ ወስመ-ጥምቀታ፡ "ክብረ-ድንግል" እና ከታናሽዬው ሚስት፡ ከሓኪም ቤዛዊት ስንሻው፣ ወስመ-ጥምቀታ ዕሴተ-ገብርኤል ጋር፡ ለዚህ ተልእኮ መመረጣቸውና መብቃታቸው፣ እየራሳቸውንም፡ ለዚህ ምርጫና ተልእኮ ማብቃታቸው፡ ምክንያቱ፡ በእኛ ዘንድ የታወቀ ቢኾንም፡ ይህንኑ እውነታ፡ እናንተም ስታውቁት፡ ለእናንተም የሚያስደንቃችሁ አይኾንም። በቂ መነሻ ያለው ነውና። ያንንም መነሻ ምክንያት፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል እገልጥላችኋለሁ፡-

እናንተ፡ የዛሬዎቹ ትውልድ፡ በደርግና በአኹኖቹ መንፈሳውያን እና ሥጋውያን ገዢዎቻችሁ፡ እየተቀጣችሁ እንደምትገኙ ኹሉ፡ እንዲሁ ደግሞ፡ በዚችው አገር፡ በስሜ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ተብለው የተጠሩ ምዝላቶቻችሁ፡ ከዛሬ አንድ ሽህ ዓመታት በፊት፡ በ፲ኛው ምእት ክፍለ-ዘመን፣ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ በፈጸሙት የክህደትና የዓመፅ፣ የአምልኮ አመንዝራነትና ልዩ ልዩ የክፋት ኃጢኣታቸው ምክንያት፡ "ዮዲት" [ይሁዲት]፥ በሕዝባዊ አጠራርም፡ "ጉዲት"፥ ወይም "እሳቶ" የተባለች፡ እጅግ ጨካኝ የኾነች ሴት ገዢ ተነሥታ፡ ተገቢውንና አስፈላጊውን የቅጣት ፍዳቸውን እንዲቀበሉ የምታደርግበት ጊዜ ነበር።

በዚያም ዘመን፡ በምድር ላይ፡ በዘመነ ኦሪቱ፡ በተለይ፡ የእኔ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ አርአያ ምሳሌ ኾና የኖረችው፡ የታቦተ-ጽዮንና የጽላተ-ኪዳኗ፡ ቅዱስ ቅርስ፡ በአኵስም ቤተ-መቅደስ፡ ይገኝ ስለነበረ፤ ያንን፡ የቅዱሱን ኪዳን ቅርስ፡ ከዚችው፡ ከይሁዲቷ የጥፋት ሰይፍ ለማዳን፡ ታማኞቹ የቅዱሱ ቅርስ ጠባቂዎች፡ ቅርሱን ይዘው፡ በዚያ ጊዜ፡ እጅግ የራቀ ኾኖ ወደሚገኘው፡ ዛሬ፡ "ደብረ-ጽዮን"፤ በሕዝባዊ አነጋገርም፡ "ደብረ-ጮን" ወደምትባለው፡ ወደአንዲቷ የዙዋይ ደሴት ሸሽተው መጡ። በዚያም፡ አሳዳጂቱ ገዢ፡ ጉዲት እስከትሞት ድረስ፡ ለ፵ ዓመታት ከቆዩ በኋላ፡ ጥቂቶቹ፡ የቅዱሱን ኪዳን ዋና ቅርስ ይዘው፡ ወደአኵስም ሲመለሱ፡ አብዛኞዎቹ፡ የቀረውን የቅዱሱን ኪዳን ቅርስ እንደያዙ፡ በዚችው ደሴት ላይ የመሠረቱትን ኑሮ ቀጠሉ።

በመልከ-ጼዴቅ ቃል-ኪዳን አማካይነት፡ ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር በወረሱት ጸጋና በረከት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን ኾነው፡ በዚሁ ልጅነትና ኪዳናዊነት፤ ክህነትና ነጋሢነት፡ እንዲህ፡ በእውነትና በቅንነት፤ በትጋትና በታማኝነት እያገለገሉን ያሉት፡ ሀብተ-ማርያምና አክሊለ-ሰማዕት፡ የእነዚያ፡ የታቦተ-ጽዮንና የጽላተ-ኪዳኗ፡ ቅዱስ ቅርስ ጠባቂዎችና ባለአደራዎች ዘሮች ከኾኑት፡ ከልጆቻችን፡ ከመምሬ መልአኩ ገብረ-ማርያም እና ከእመቤት ብርዝነሽ ከፈኒ፡ በዚችው ደሴት ላይ፡ በሰውነት ተወልደውና በመልካም አድገው፥ በመንፈስ-ቅዱሳዊው ዕውቀት ታንፀውና በሥጋዊው የሕክምና ሙያ ተመርቀው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዜግነትና ሓዋርያነት እንዲበቁ ያደረግናቸው፡ ተወዳጆች ልጆቻችን ናቸው።

ቀደም ብዬ፡ እኒህ ኹለት ኪዳናውያን ወንድማማች፡ ለዚህ፡ ለዛሬው ማንነታቸው በቅተው እንዲገኙ ያደረጋቸውን እውነታ፡ "እናንተም ስታውቁት፡ ለእናንተም የሚያስደንቃችሁ አይኾንም።" ያልሁት ለዚህ ነው።

**ተዐውደ፡ በሓምሌ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፬ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፤
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ \+ \+